# ባጠቃቀም ብልሹነት የምንቸገርባቸው የጸጋ ስጦታዎች

ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፣ አገልጋዮችና

በሳል አባላት የቀረበ ብርቱ ማሳሰቢያ

ከዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ

"ኤክሌሺያ ተነሺ!" አገልግሎት

ብርሃነ ወንጌል መጥምቃዊያን ቤተ ክርስቲያን የለየችው
ለተሃድሶና ደቀ መዛሙርትን ለማፍራት ቤተ ክርስቲያንን
የሚያነሳሳና የሚያስታጥቅ አገልግሎት

የመጀመሪያ እትም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

Copyright - 1994 ዓ.ም.

“ኤክሌሺያ ተነሺ!” አገልግሎት
መ.ሣ.ቁ. 5903 ስልክ 632057

ተለይቶ ካልተገለጸ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት
ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው። (ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር 1993 ዓ.ም.)



# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ሸክምን በልቤ አስቀምጦ ፣ የቃሉን ማስተዋል ሰጥቶኝ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ለረዳኝና ላተጋኝ ከሁሉ በላይ ለሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ዶ /ር አታላይ ዓለም ፣ ወንጌላዊ ደሳለኝ ደምሴ ፣ ወንደም ንጉሤ ቡልቻና ዶ /ር አያልነሽ መንገሻ ረቂቁን አንብበው አስፈላጊ ማስተካከያዎችን አድርገዋል። “ኤክሌሺያ ተነሺ!” አገልግሎትን በጸሎት የሚደግፉ ወገኖች ስለሥራው ጸልየዋል ፣ እንድገፋበትም አበረታትተውኛል። ረቂቁን በኮምፒዩተር በማዘጋጀትና የተዛነፉ አገላለጾችንም በማረም ውድ ባለቤቴ ሲ /ር አልማዝ ታረቀኝ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጋለች። እነዚህን ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካቸው ፣ ብድራታቸውንም በበጎነቱ ይክፈል።

ዶ /ር ብርሃኑ ሀብቴ

## ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 5 |
| I. የጸጋ ስጦታዎች አጠቃላይ ባሕርያት | 7 |
| II. የልሳንና የትንቢት ስጦታዎች አጠቃቀም | 13 |
| III. የዕውቀትን ቃል መናገርና የፈውስ ስጦታዎች | 28 |




# መግቢያ፡- ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ያለችበት አደጋ

የአዲስ ኪዳን ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ነው። ገና ከጅማሬው ፣ ደቀ መዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከመቀበላቸው በፊት የአገልግሎት እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ጌታ ከልክሏቸው ነበር[1]። በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ይፋ የሆነውን አገልግሎቷን የጀመረችው በበዓለ ሃምሳ ቀን ከተከሰተው ከመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጋር ነበር።

መደበኛው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚኪያሄደው መንፈስ ቅዱስ ለምእመናን በሚሰጠው የጸጋ ስጦታ ነው። ወንጌልን መስበክ ቢሆን ፣ ቃሉን ማስተማር ቢሆን ፣ ቤተ ክርስቲያንን መምራት ቢሆን ፣ ምእመናንን መምከርና ማጽናናት ቢሆን ፣ የዝማሬ አገልግሎት ቢሆን ፣ እያንዳንዳቸው የሚከናወኑት በጸጋ ስጦታዎች ነው። እነዚህንና ፣ የበለጠ ተዓምራዊ የሚመስሉትን ፣ ልሳን ፣ ትንቢት ፣ ፈውስን ፣ ወዘተርፈ ጨምሮ ወደ 28 የሚደርሱ የጸጋ ስጦታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል። ከዚህ የተነሳ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የአዲስ ኪዳንን አገልግሎት እንደሚከተለው የገለጸው፡-

> *"እናንተ በቀለም ሳይሆን በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ በድንጋይ ጽላት ሳይሆን በሰው ልብ ጽላት ላይ የተጻፋችሁና በእኛ የተገለገላችሁ የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤዎች ናችሁ... እርሱም በፊደል ላይ ሳይሆን በመንፈስ ላይ የተመሠረተውን የአዲሱ ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን ፣ ምክኒያቱም ፊደል ይገድላል ፣ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።"*
> *(2ቆሮ 3:3 ፣ 6)*

እንግዲህ የጸጋ ስጦታዎች ይህን ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ከሆነ በማስተዋል ልንጠቀምባቸው ግዴታ ይሆናል። ለሙሴ እንኳን የብሉዩን ኪዳን አገልግሎት አስመልክቶ ፣ "በተራራው ላይ በተገለጠልህ ምሳሌ መሠረት ሁሉን ነገር እንድታደርግ ተጠንቀቅ"[2] የሚል የማያወላዳ ትእዛዝ ተሰጥቶት ነበር። የአዲስ ኪዳንን የሕይወት አገልግሎት ለምንሰጠው ለእኛማ ጥንቃቄው ምን ያህል ይበረታ! ሙሴ በተራራው ላይ የሚያየው ሞዴል ተገልጦለት ነበር ፣ ለእኛ ደግሞ የተብራራው የአዲስ ኪዳን ቃል ተገልጦልናል። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደመከረው ይህን ቃል "በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት ጥንቃቄ እንደሚደረግ"[3] ልንጠነቀቅለት ይገባል። ይህን አቋም ቸል ካልን መብራቱ ይጠፋብንና በጨለማ እንርመሰመሳለን።

ዛሬ በየቤተ ክርስቲያናችን ያለው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው። ከጸጋ ስጦታዎች ብዙዎቹ በመካከላችን እየሠሩ አይደሉም። እየሠሩ ናቸው የሚባሉትም ፣ በአብዛኛው አጠቃቀማቸው የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት ስለሚተላለፍ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመፈጸማቸው ምንም ዋስትና የለም።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከራሱ ቃል ውጪ ስለማይሠራ ፣ ቃሉን የሚተላለፍ የጸጋ ስጦታ አጠቃቀም ከመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን በአገልጋዩ የስሜት ግፊት የሚገለጥ ነው ብለን ለማመን ግድ ይሆንብናል።

ከቃሉና ከመንፈስ ቅዱስ አሠራር ውጪ የሚደረግ ልምምድ ከፍተኛ አደጋዎች አሉት። በመጀመሪያ ደረጃ ለዚህ ዓይነቱ ልምምድ የሚጋለጡት ሰዎች ፣ በተለይም ጌታን የማያውቁት ፣ ሊሰናከሉ ይችላሉ። በቀጣይ ደረጃ ደግሞ ፣ እግዚአብሔር ባላለው ነገር ላይ በተደጋጋሚ የሚሰጥ ተስፋ ወደ ፍጻሜ ስለማይመጣ ክርስቲያኖች በጸጋ ስጦታዎች ላይ ያላቸው አመኔታ ይመነምናል። ምእመናን ወደዚህ ደረጃ እንዲወርዱ ከተደረገ በትክክል የሚገለጥ ጸጋን እንኳን ለመቀበል ይቸገራሉ። ከሁሉ የሚብሰው አደጋ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ማዘን ነው[4]። ለዚህ ይሆናል የጸጋ ስጦታዎች ሊገለጡ በሚገባቸው መጠን ዛሬ የማይገለጡት።

በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ የምናተኩርባቸው የጸጋ ስጦታዎች በአጠቃቀም ላይ ብዙ የምንቸገርባቸው ፣ የልሳን ፣ የትንቢት ፣ እውቀትን የመናገርና የፈውስ ስጦታዎች ይሆናሉ። አቀራረቡ ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ይመሠረታል። አንባቢዎቼ እንደቤሪያ ሰዎች ልበ ሰፊ በመሆን ቃሉን በጸሎት መንፈስ በመሆን እያገናዘቡ ለተገለጠው እውነት ተገዢ ይሆናሉ ብዬ እጠብቃለሁ። አገልጋዮችና ምእመናን በእግዚአብሔር ቃል መንገድ እንዲራመዱ ማስተማር ፣ መምራትና ማረም የመሪዎችና የእረኞች ኃላፊነት ስለሆነ የዚህችን መጽሐፍ መልእክት መሪዎችና እረኞች በጥንቃቄ እንዲገነዘቡልኝ አደራ እላለሁ።

---

## ማስታወሻ

1. ሉቃስ 24 ፡ 49
2. ዕብራውያን 8 ፡ 5
3. 2ኛ ጴጥሮስ 1 ፡ 19
4. ኤፌሶን 4 ፡ 30 ፣ 1ኛ ተሰ 5 ፡ 19



# I. የጸጋ ስጦታዎች አጠቃላይ ባሕርያት

የያዝነውን ርዕስ በጥሩ እንድንገነዘበው የሚረዱንን የጸጋ ስጦታዎች ባሕርያት በነጥቦች እያስቀመጥሁ በጥቂቱ እዘረዝራቸዋለሁ፦

## ሀ) ዳግም የተወለደ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ የጸጋ ስጦታ ይቀበላል (ሐሥ 2 ፡ 38 ፣ 1ኛ ቆሮ 12 ፡ 7 ፣ 1ኛ ጴጥ 4 ፡ 10)

አንድ አካል በቅንጅት በሚሠሩ ብዙ ብልቶች እንደሚንቀሳቀስ ሁሉ የክርስቶስም መንፈሳዊ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ልትንቀሳቀስ የሚገባት በምእመናኑ ውስጥ በተቀመጡ የጸጋ ስጦታዎች የተቀናጀ አሠራር ነው። በመግቢያው ላይ እንደጠቀስኩት ፣ የጸጋ ስጦታ ያልተመደበለት መንፈሳዊ አገልግሎት የለም። ይህ ማለት የጸጋ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን ሕልውናና ዕድገት ያስፈልጋሉ ማለት ነው። ለዚህም ነው ለእያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚሰጠው። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የሚሰጠው ክርስቲያን ለሠራው መልካም ሥራ ሽልማት አድርጎ አይደለም። እርሱ ሌሎች በተሰጣቸው ጸጋ እንደሚገለገል ሁሉ ሌሎችን እንዲያገለግልበት ነው እንጂ።

የጸጋ ስጦታን ለመቀበል የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ዳግም መወለድና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ብቻ ናቸው። ከዚህም የተነሳ በክርስቶስ ጀማሪ የሆነ ሰው የጸጋ ስጦታ ሊቀበል ይችላል ማለት ነው። በውስጡ የተቀመጠው ጸጋ ታላላቅ ተአምራዊ ሥራዎችን ሊሠራ ይችላል። ሆኖም ግን አማኙ ዕለታዊ የክርስትና ልምምዶችን እንኳን በሚገባ ያላወቀ ሊሆን ይችላል። አስደናቂ ጸጋ በሰው ውስጥ ስለተገለጠ አማኙ ከፍተኛ የሕይወት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ሊሰማው አይገባም። መሪ አገልጋዮችም ይህን ሰው መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ከማስተማር ሊዘናጉ አይገባም።

ቤተ ክርስቲያን እንድትታነፅ እያንዳንዱ አማኝ በተቀበለው ከሌላው የተለየ ጸጋ አካሉን ማገልገሉ አስፈላጊ ነው። ሁሉ የጸጋ ስጦታዎች በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ቢሠሩ ግን አንዱ በሌላው የሚገለገልበት ሁኔታ አይኖርም ማለት ነው። ይህ ደግሞ መሠረታዊ የሆነውን የክርስትናን ብልታዊ ግንኙነት ያፋልሳል። ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ ሊሰመርበት የሚገባው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ተቀብሎ በዚያ ጸጋ ሌሎችን ማገልገል የክርስቲያን መደበኛ ኃላፊነት መሆኑን ነው። ከመደበኛው ለየት ባለ መልኩ ፣ ብዙ ኃላፊነት ላለባቸው አገልጋዮች በርከት ያሉ የጸጋ ስጦታዎች ሊሰጣቸው ይችላል። ጌታ ኢየሱስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ በምድር ያሳለፈውን ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ሙላት እንደተመላለሰ ፍጹም ሰው ሕይወት አድርገን ብንረዳው ፣ አገልግሎቱ የብዙ ጸጋዎች መግለጫ እንደሆነ ልናስተውል እንችላለን። ነቢዩ ኢሳይያስም ስለእርሱ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ ፣ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት

መንፈስ ያርፍበታል" ብሏል (ኢሳ 11 ፡ 2)። ሐዋርያትም በእያንዳንዳቸው ላይ በርከት ያሉ ጸጋዎች ተገልጠውባቸዋል[2] ፤ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር ፤ ያስተምሩ ነበር ፤ ይፈውሱ ነበር ፤ ተአምራትን ያደርጉ ነበር ፤ ይመሩ ነበር። መናፍስትን መለየት ፤ እውቀትን መናገር ፤ ጥበብን መናገር ፤ ወዘተርፈ ፤ በተለያዩ ጊዜያት ተገልጠውባቸዋል። እንግዲህ በአንድ ሰው ሕይወት ብዙ ጸጋዎች ተገለጡ ማለት ብዙ ኃላፊነት በላዩ ተሸክሟል ማለት እንጂ እግዚአብሔር የተለየ ሞገስ ሰጥቶት ከፍተኛ ክብርን አጎናጽፎታል ማለት አይደለም።

## ለ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና የመንፈስ ፍሬ ተደጋጋፊ ግንኙነት አላቸው (1ኛ ቆሮ 13 ፡ 1 - 7)

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የክርስትና ሕይወት ብስለት መግለጫ እንዳልሆኑ ተመልክተናል። በአንጻሩ ግን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በሙላት ሲታይ የክርስትና ሕይወት ብስለትን በትክክል ያሳያል። የመንፈስ ፍሬ ዝርዝር ባሕርያትን ምንነት ስናጤን የክርስቶስ ባሕርያት መሆናቸውን እናስተውላለን[3]። የመንፈስ ፍሬን የማፍራት ሂደትና ክርስቶስን የመምሰል ሂደት አንድ ናቸው። ጌታ እንዳስተማረው ፤ የመንፈስ ፍሬ የሚገኘው በክርስቶስ ውስጥ በእምነት ጸንቶ በመቆየትና በፍቅር ቃሉን እየታዘዙ በመመላለስ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሂደት ሲገልጸው … "ይልቁንም ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስህን አሠልጥን" (1ኛ ጢሞ 4 ፡ 7) በማለት ከፕሮፌሽናል የስፖርት ልምምድ ጋር አመሳስሎታል። ክርስቲያን በየእለቱ በንስሐ እየተመላለሰ ራሱን ለቃሉ ሲያስገዛ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ባሕርይ በውስጡ ይቀርጻል።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ተደጋጋፊ ሥራ ይሠራሉ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መሠረታዊ ዓላማ ቅዱሳንን ለማነጽ ስለሆነ ለክርስትና ሕይወት ዕድገት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ይህ አሠራር ከየትኛውም የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ይልቅ በኤፌሶን 4 ፡ 11 - 13 ውስጥ በግልጽ ይታያል። በመጀመሪያ ደረጃ አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች ምእመናንን ለአገልግሎት ያዘጋጃሉ። ምእመናን ሁሉ በዚህ መልኩ እንደየጸጋቸው ከሠለጠኑ በኋላ የየበኩላቸውን አስተዋፅዖ ሲያደርጉ የሚገኘውን ፍሬ ቁጥር 13 ያሳየናል፦

*"ይህም የሚሆነው ፤ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው።"*

በአንጻሩ ደግሞ የመንፈስ ፍሬ በክርስቲያን ሕይወት ሲሞላ የጸጋ ስጦታዎች በአግባቡ ተግባራዊ ይሆናሉ። የ1ኛ ቆሮንቶስ 13 መልዕክትም ይኸው ነው።



በዚህ ምዕራፍ የፍቅር ባሕርያት ሲዘረዝሩ (ቁጥር 4 - 7) ፤ ከመንፈስ ፍሬ ባሕርያት ጋር በጣም ተመሳሳይ ሆነው እናገኛቸዋለን።

## ሐ) የጸጋ ስጦታዎች ተግባራዊ የሚሆኑት በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነው

ከመነሻው ፤ ስጦታዎችን እንደፈቃዱ የሚያደላድለው መንፈስ ቅዱስ ነው[4]። ለማን ምን ዓይነት ስጦታ እንደሚሰጥ መመዘኛው በእርሱ እጅ ነው ያለው። ለትናንሽ ብላቴኖች ታላላቅ ራዕዮችን ሲያሳይ እንደነቃለን። ምንም የቀለም ትምህርት ለሌላቸው የወንጌል ሰባኪነት ታላቅ ጸጋ ሲሰጥ አይተን እንገረማለን። ምናልባት የራሳችንን የሕይወት ዝግጅት በጥሩ ሁኔታ የገመገምን መስሎን ፤ የተወሰነ የጸጋ ስጦታ ቢኖረን መልካም ነው ብለን እናስብ ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ ግን በማናችንም ግምት ላይ ሳይደገፍ ለራሱ እውቅ በሆነ ትክክለኛ ሚዛን እየመዘነ ለእያንዳንዱ አግባብነት ያለውን ስጦታ ይሰጣል።

ስጦታዎችን እንደፈቃዱ መለገስ ብቻ አይደለም ፤ የተሰጠ ስጦታም ተግባራዊ የሚሆነው በወቅቱ መንፈስ ቅዱስ ሲመራና ሲያነሳሳ ነው። ግለሰቡ በመረጠው ጊዜ እንደፈቀደ ሥራ ላይ ሊያውለው አይችልም። ጌታችን ኢየሱስ የመፈወስ ፤ ድንቆችና ተዓምራትን የማድረግ ስጦታ ነበረው። ሆኖም ግን ለመፈወስ የመንፈስ ቅዳስ ኃይል በትኩሱ በውስጡ ሊንቀሳቀስ አስፈላጊ ነበር[5]። ሐዋርያው ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ለተሰበሰበው ሸንጎ ሲናገር እንደገና በትኩስ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። ወቅታዊ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ነው በውስጡ ያለው ጥበብን የመናገር ስጦታ በሸንጎው ላይ ውጤታማ እንዲሆን ያደረገው[6]። ሐዋርያው ጳውሎስ በበርያሱስ ላይ የፍርድ ተአምርን ባደረገ ጊዜም እንደገና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። እንግዲህ የጸጋ ስጦታን የሚለማመድ ክርስቲያን ስጦታውን ተግባራዊ ለማድረግ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ወይም በመንፈሱ ውስጥ የሚታወቀውን እንቅስቃሴ መጠበቅ አለበት ማለት ነው። በልሳን የሚናገር በፈቀደው ጊዜ ሊናገር ቢሞክር እንደዚሁ በልማድ ከንፈሮቹን ያንቀሳቅሳል ፤ ጸሎቱም የማነፅ ኃይል አይኖረውም። የትንቢት ስጦታ ያለውም ሁኔታዎችን ገምግሞ ፤ በስሜቱ ተነሳስቶ "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል" በማለት ለጉዳዩ መልስ ለመስጠት ቢሞክር እግዚአብሔር ቃሉን አያጸናለትም።

## መ) የጸጋ ስጦታዎች በአእምሮ ይመዘናሉ (ሮሜ 12 ፡ 3 - 6)

የጸጋ ስጦታዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ይህ ቃል ቁልፍ ነው። የጸጋ ስጦታን የተቀበለ ግለሰብ አእምሮውን ከፍቶ ራሱን እንዲመዝን ይህ ቃል ይመራል። ሃሳቡን ብናሰፋው ፤ ተመሳሳይ መመዘኛ የሚጠቀሙ ሌሎች ግለሰቦችም የሌላን ሰው የጸጋ ስጦታ በአእምሮ ሊመዝኑት ይችላሉ ማለት ነው። አንድን ነገር በአእምሮ መገምገም የሚቻለው ስለጉዳዩ በማስረገጥ የተነገረውን ከተገኘ ውጤት ጋር በማገናዘብ ነው። አስቀድሜ እንደገለጽኩት የጸጋ

ስጦታዎች መንፈሳዊ የአገልግሎት መሣሪያዎች ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእነርሱ ስለሚገለጥ የሚታይ ውጤት ይኖራል። ወንጌልን የመስበክ ጸጋ ያለው ሰው ላላመኑ ሰዎች ወንጌልን ሲያቀርብ ፣ ጸጋው ከሌለው ሰው ይልቅ በርከት ያሉ ሰዎችን ወደክርስቶስ እንዲያመጣ ይጠበቃል። የመፈወስ ጸጋ ያለው ሰው ለታመሙ ሰዎች ሲጸልይ ፣ ለመፈወስ የእግዚአብሔር ሰዓት እስከሆነና የሚጸለይላቸው ሰዎች ስለእምነት አስፈላጊው መመሪያ እስከተሰጣቸው ድረስ ፣ ከተጸለየላቸው አብዛኞቹ እንዲፈወሱ ይጠበቃል። የሐዋርያት ዘመን አገልግሎት ይህን እንደሚመስል እናውቃለን።

ሰው ግን የማስተማር ስጦታ አለኝ ብሎ ቢያስብ ፣ ነገር ግን ለማስተማር በቆመ ቁጥር አዘውትሮ ሰዎችን ግራ የሚያጋባ ቢሆን መንፈስ ቅዱስ በማስተማር ጸጋ እየተጠቀመበት ነው ማለት ይቻላል? ምንም ጸጋ ሳይጨመርበት ፣ ከጥሩ ሥልጠና በኋላ ፣ ትውልዶችን በስነ-ሥርዓት የሚያስተምሩ ሰዎች እኮ ሞልተዋል። ወይም የመምከር ጸጋ አለኝ የሚል ፣ ነገር ግን አንድንም ሰው ወደ ቀና መንገድ ባይመልስ ፣ የተጣሉ ሰዎችን ከማቀራረብ ይልቅ የሚያራርቅ ቢሆን ይህ ሰው የመምከር ጸጋ አለው? ጥሩ ምክር የሚሰጡ ጌታን የማይከተሉ ሰዎች እንዳሉም እናውቃለን። እረኛ (Pastor) ነኝ የሚል ፣ ግን ምእመናን አዘወትረው የሚሸሹትና ፣ አብረውት የሚያገለግሉት አጠገቡ ሲቀርቡ የመሸማቀቅ ስሜት የሚሰማቸው ቢሆን የእረኝነት ጸጋ ሊኖረው ይችላል?

እንግዲህ የጸጋ ነገር ከተነሳ ፣ ሥራውን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ በሰው ጥረት ከሚገኝ ውጤት እጅግ የላቀ ውጤትን ልናይ ይገባል ማለት ነው። ይህ ግንዛቤ ነው ግለሰቡ ራሱም ሆነ ፣ አገልግሎቱን የሚከታተሉ ሌሎች ፣ በትክክለኛ ሚዛን ጸጋውን እንዲመዝኑ የሚያስችላቸው። በዚህ ነጥብ ላይ የማያወላዳ አቋም ከያዘን ግለሰቦችም ሆኑ ቤተክርስቲያን ከብዙ ችግር ይተርፋሉ።

## ሠ) እግዚአብሔር ስለጸጋ ስጦታው አይጸጸትም (ሮሜ 11 ፡ 29)

አብዛኛውን ጊዜ ሰው ስጦታን የሚሰጠው ለተቀበለው አገልግሎት ምስጋናን ለማቅረብ ሲፈልግ ወይም ለወደፊት ጥቅም ውለታን ለማስቀጠር ሲያስብ ነው።
በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ቢበላሽ ፣ ሰጪው ስለሰጠው ስጦታ ይጸጸታል ፣ የሚያመቸው ከሆነም የሰጠውን ስጦታ መልሶ ይወስደዋል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርም በዚህ ዓይነት የሚሠራ ይመስለናል። እግዚአብሔር ግን ፣ በተለይ የጸጋ ስጦታዎችን አስመልክቶ ፣ የሚሰጥበት ዓላማ ሰው ለሰው ስጦታ ከሚሰጥበት ዓላማ የተለየ ነው። የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የእግዚአብሔርን ልግስና እንጂ የተቀባዩን ብቁነት አያመለክትም። ከዚህም የተነሳ የተቀባዩ የሕይወት አቋም ለውጥ ሲኖር እግዚአብሔር ተሸቀዳድሞ ስጦታውን አይወስድም።



በርዕሱ ላይ የጠቀስሁት ቃል የእስራኤልን መጠራትና ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የሚያመለክት ነው። እንደተከታይ የእስራኤል ትውልዶች በደል ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር አፋጣኝ እርምጃ የፍርድ እርምጃ ሊሆን ይገባው ነበር። እግዚአብሔር ግን ስለመጥራቱና ስለጸጋ ስጦታው የማይጸጸት ስለሆነ ፣ ምክኒያት እየፈለገ በዘመናት ሁሉ ይታደጋቸው ነበር። ቅጣትን በእነርሱ ላይ ቢያመጣም ጨርሶ ሊያጠፋቸው ሳይሆን ስህተታቸውን ተገንዝበው ወደእርሱ እንዲመለሱ ለማድረግ ነበር። በጠቀስነው ምዕራፍ ውስጥ እንደምናነበውም ፣ በአሕዛብ ላይ የተገለጠው የማዳን ጸጋ ፣ ከእስራኤል አኳያ እነርሱን በማስቀናት ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ለማድረግ ነው። ዛሬም እግዚአብሔር ስለሰጠው የጸጋ ስጦታ አይጸጸትም። ጸጋ የተቀበለ ሰው ሕይወቱ ችግር ውስጥ ቢገባ ከችግሩ እስኪወጣ ድረስ ይታገሰዋል ፣ ከችግሩ እንዲወጣም ይረዳዋል። በዚህ የሽግግር ወቅት ሁሉ የጸጋ ስጦታ በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ ሊቀጥል ይችላል። እዚህ ላይ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ የጸጋውን ስጦታ ከሰውየው ሕይወት ለይቶ ማየቱ ነው። እግዚአብሔር እየተጠቀመበት ነው ብሎ በሰውየው ሕይወት የሚገለጠውን ስህተት ሁሉ አብሮ መቀበል ትክክል አይሆንም።

---

## ማስታወሻ

1. 1ኛ ቆሮ 12 ፡ 27 - 31 ፣ 14 ፡ 12
2. ሮሜ 15 ፡ 18 - 19 ፣ 2ኛ ቆሮ 12 ፡ 12
3. ገላ 5 ፡ 22
4. 1ኛ ቆሮ 12 ፡ 11
5. ሉቃ 5 ፡ 17
6. ሐሥ 4 ፡ 8 - 22

# II. የልሳንና የትንቢት ስጦታዎች አጠቃቀም

ልሳንና ትንቢት በየቤተክርስቲያኑ በብዛት የሚገለጡ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው። አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ግን ብዙ ስህተት ይደረጋል። ያለትርጉም በጉባኤ በከፍተኛ ድምፅ የሚነገር ልሳን የማያምኑ ሰዎችን የሚያስናክልና የሚያሸሽ ሆኗል። ቃሉን የሚያውቁ አማኞችም ጥያቄ እያነሱ የመለያየት ምክኒያት ሆኗል። ከእግዚአብሔር ቃል መመሪያ ውጪ የሚነገሩ ትንቢቶች ደግሞ የብዙ የዋህ ክርስቲያኖችን ሕይወት ለጉስቁልና ዳርገዋል። “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል!” በሚል ኃይለ ቃል ስለሚነገሩ ያለምንም ማገናዘብ መቀበል እንዳለባቸው ይመስላቸዋልና። በአንጻሩ ደግሞ ጤናማ የሆኑ ትንቢቶች በአግባቡ የሚነገሩበት መድረክ ካለመፈጠሩ የተነሳ አገልጋዮች ተስፋ ቆርጠዋል ፣ በረከትም ቀርቷል።

በተለይ የነዚህን ሁለት የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም በሚመለከት በዓላማ የተጻፈ የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ስላለ የጠቀስኳቸውና ሌሎች መሰል ችግሮች መፈጠራቸው አስፈላጊ አይሆንም። የቃሉ መመሪያ እያለን እስከዛሬ ለምን ግራ መጋባት ይኖራል? ይህ የሆነበት ሁለት መሠረታዊ ምክኒያቶች ይታዩኛል። አንደኛው መጽሐፍ ቅዱስን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የመፍታት ዘዴ በስፋት አለመታወቁ ነው። ከዚሁ ጋር ደግሞ ፣ ቃሉን መሻር ፍጹም አደገኛ የሆነ እርምጃ መሆኑን በጥልቀት አለመገንዘብም አለ። ሁለተኛው ምክኒያት ፣ ሥርዓትን በማስያዝ ረገድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነታቸውን አለመገንዘባቸው ወይም ተገንዝበው ቸል ማለታቸው ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 እና ምዕራፍ 14 ፣ ከያዘነው ርዕስ አኳያ በጥንቃቄ አጥንተን ግልጽ የሆነ ሃሳብ እንጨብጣለን ብዬ አምናለሁ። የቃሉን መሠረት ከያዘን ቤተ ክርስቲያን በነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ስም ለሚመጣ ችግር ሰለባ ከመሆን ተርፋ ተጠቃሚ ትሆናለች።

## ሀ) የጥናቱን ክፍል (1ኛ ቆሮ 12 - 14) የመፍታት መርህ

እንደሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ሁሉ የ1ኛ ቆሮንቶስ መልዕክትም ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ደብዳቤ ነው። ማንኛውም ደብዳቤ የሚጻፍበት የራሱ ምክኒያት አለው። የደብዳቤው ጸሐፊ ጊዜ ወስዶ ሲጽፍ ለተከሰተው ጉዳይ መልስ ወይም መፍትሔ ለመስጠት ዓላማ አድርጎ ነው። በተለይም በሐዋርያው ጳውሎስ ዘመን የጽሕፈት መሣሪያዎች እንደልብ ስለማይገኙና ፣ ደብዳቤ መላክም እንደ ዛሬው ቀላል ስለማይሆን ፣ የሚጻፍ ደብዳቤ የሚፈለገውን መልዕክት በማስተላለፍ ግቡን እንዲመታ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል ብዬ አምናለሁ። ባጭሩ ለማስቀመጥ ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ በተነሱ ጉዳዮች ላይ እርስ በርሱ የማይቃረን ግልጽ መመሪያ ይሰጣል ብለን እንጠብቃለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈበትን መንፈስ ተረድተን በርዕሳችን ላይ ማትኮር እንዲያመችን ፣ የመልዕክቱን መነሻ ምክኒያቶች ባጭሩ መቃኘት ይጠቅማል። መልዕክቱን ለመጻፍ ያበቁት መረጃዎች የመጡት ከሁለት ምንጮች ነበረ። የመጀመሪያው ምንጭ ከቀሎኤ ቤተሰብ በቃል የተሰማው ነው (1 ፡ 11)። ከዚህ ምንጭ የተገኘው የመጀመሪያው ጉዳይ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተከሰተው መከፋፈል ሲሆን ፣ በተጨማሪም የአባቱን ሚስት ስላገባው ሰው (5 ፡ 1) ፣ ክርስቲያኖች ተካሰው በዓለም ፍርድ ቤት መቆማቸው (6 ፡ 1) እና በመካከላቸው ስለተንሰራፋው ዝሙት (6 ፡ 12 - 13) ተረድቷል። ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 6 መጨረሻ ድረስ ያለው የመጽሐፉ ክፍል እነዚህን መነሻ ምክኒያቶች በተመለከተ ትምህርት ፣ ተግሣጽና ውሳኔ የሚሰጥ ነው። አከታትለን ስናነበው እንደምናስተውለውም ፣ ሃሳቦች የተገለጡት ሥርዓት ባለው ቅደም ተከተል እየተቋጩ ነው።

ሁለተኛው የመረጃ ምንጭ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ለሐዋርያው የተጻፈ ደብዳቤ ነበረ (7 ፡ 1)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጋብቻ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሚዛናዊ መልስ ከሰጠ በኋላ ወደሌሎች ጥያቄዎቻቸው በመሻገር ፣ ለጣዖት የተሰዋ ሥጋን በተመለከተ (8 ፡ 1 - 11 ፡ 1) ፣ በአምልኮ ወቅት ሴቶች ራሳቸውን ስለመሸፈናቸው (11 ፡ 2 - 16) ፣ በጌታ እራት አከባቢ ስለተፈጠረ ችግር (11 ፡ 17 - 34) ፣ ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች (ቁ 12 ፡ 1 - 14 ፡ 40) እና ስለሙታን አካላዊ ትንሳኤ (15 ፡ 1 - 58) ጽፎላቸዋል። ይህንንም ክፍል አያይዘን በእርጋታ ስናነበው ፣ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ በቤተ ክርስቲያኑ አባላት መካከል የተለያየ አመለካከት ተፈጥሮ ፣ የሚያስተራርቃቸውን እውነት ለማግኘት ለሐዋርያው እንደጻፉለት ማስተዋል እንችላለን። ክርስቲያን ሚስት ያግባ ወይስ ባያገባ ይሻላል? ለጣዖት የተሰዋ ሥጋ ቢበላስ? ሴቶች በአምልኮ ወቅት ራሳቸውን ባይሸፍኑስ? የሚሉ ዓይነት ክርክሮች ሳይነሱ አልቀረም። የጌታ እራትን በተመለከተም ሀብታሞቹ የራሳቸውን ቡድን አቋቁመው ይሰክሩ ነበር ፣ ድሆቹ ደግሞ የሚቀምሱትን ያጡ ነበር።

የጸጋ ስጦታዎችንም በተመለከተ የተጻፈው ክፍል በርዕሱ ላይ መደበኛ ትምህርት ለማስተማር አልነበረም። ዓላማው ያ ቢሆን ኖሮ በተጠቀሱትና በሌሎችም የጸጋ ስጦታዎች ላይ የተሟላ ትምህርት በተሰጠ ነበር። በምዕራፍ 12 ውስጥ 13 ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች በስም ተጠቅሰዋል ፣ ሆኖም ግን ስለየትኛቸውም ዝርዝር ሃሳብ አልተገለጸም። ምዕራፉ ያተኮረው የጸጋ ስጦታዎች የሚሰጡት ለጋራ ጥቅም መሆኑንና (ቁ 7) ፣ ምንጫቸውም ያው አንዱ መንፈስ ስለሆነ ስጦታዎችን ማበላለጥ አግባብ እንዳልሆነ ማሳየቱ ላይ ነው (ቁ 12 - 30)። ይህ የምዕራፉ ትኩረት የሚያስገነዝበን ፣ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አባላት መካከል የጸጋ ስጦታዎችን የማበላለጥ ውዝግብ መነሳቱን ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ሐዋርያው እነዚህን ሁሉ ዐረፍተ-ነገሮች በከንቱ ባልጻፈም ነበር።



ወደ ምዕራፍ 13 ስንሻገር ፣ የመልዕክቱ አቅጣጫ ለተዛባ አሠራር እርምት ለመስጠት መሆኑ አያጠራጥረንም። የትኛውም የከበረ የሚመስለን ስጦታ ቢኖረንም ፣
ፍቅር በጎደለው ሁኔታ ብንለማመደው ምንም እንደማይጠቅም ያስረግጣል[1]። የፍቅርን መልካም ባሕርያት ሲዘረዝር ደግሞ[2] ፣ ፍቅር የጎደለው ሕይወት በአንፃሩ ምን እንደሚመስል ስለሚጠቁም ፣ ያለፍቅር የሚገለጥ የጸጋ ስጦታ ፣ አለመጥቀም ብቻ ሳይሆን ጎጂ እንደሆነም መገንዘብ እንችላለን።

በቀደሙት ሁለት ምዕራፎች ውስጥ በጥበብና በቅልጥፍና መንደርደሪያ መድረኩን ካዘጋጀ በኋላ በምዕራፍ 14 ውስጥ ዋናውን ጉዳይ በቀጥታ ይገናኘዋል። የምዕራፉ ትኩረት በግልጽ የሚያሳየን በቆሮንቶስ የተነሳው ዋናው የጸጋ ስጦታ ችግር የልሳንና የትንቢት ስጦታዎች አጠቃቀምን የተመለከተ መሆኑን ነው። ልሳንን አስመልክቶ የቆሮንቶስ ሰዎች የስጦታዎች ሁሉ አውራ እንደሆነ ቆጥረውት  ስጦታውን ለማግኘት የብዙዎች ፍላጎት ነበር (12 ፣ 18 - 20)። ለአምልኮ ሲሰበሰቡም ስጦታው ያላቸው ሰዎች ለሌሎች ስጦታዎች ቦታ ሳይሰጡ ልሳንን ሥርዓት በጎደለው መልኩ ሊጠቀሙበት ይፈልጉ ነበር (ቁ 23)። በአንጻሩ ደግሞ ፣ ለአደባባይ አገልግሎት የበለጠ የሚጠቅመውን የትንቢት ስጦታ የሚፈለገውን ቦታ አልሰጡትም (1 ፣ 5 ፣ 18 - 19)።

ስናጠቃልል ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12 - 14 የልሳንና የትንቢት ስጦታዎችን በአግባቡ ስለመጠቀም መመሪያ የሚሰጥ ክፍል ነው። ይህን ክፍል በትክክል ልንጠቀምበት የምንችለው "የእግዚአብሔር ቃል በዚያን ዘመን ለቆሮንቶስ ሰዎች ያልተናገረውን ዛሬ ለእኛ አይናገርም" የሚለውን መርህ[3] በማክበር ነው። መልዕክቱ የቆሮንቶስ ሰዎች የልሳን ስጦታን ያለተርጓሚ የማያምኑ ሰዎች ባሉበት በአደባባይ እንዳይናገሩ የከለከለ ከሆነ ዛሬ ለእኛ በተቃራኒው እንድናደርግ ሊፈቅድልን አይችልም። በዚያ ዘመን የተዛባ አጠቃቀምን ያረመ ከሆነ ፣ ዛሬም የተዛባ አሠራርን ለማረም ልንጠቀምበት አግባብ ነው። ይህን ግንዛቤ ይዘን ነው የልሳንና የትንቢት ስጦታዎችን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችለንን መመሪያ የሚከተሉት አንቀጾች ውስጥ የምናስቀምጠው።

## ለ) የልሳን ስጦታ አጠቃቀም

የልሳን ስጦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የ1ኛ ቆሮንቶስ ዋናው መልዕክት ክርስቶስን ያልተቀበሉ ሰዎች ባሉበት ስብሰባ ፣ ተርጓሚ እስከሌለ ድረስ ፣ ልሳን ለሌላው በሚሰማ ድምፅ እንዳይነገር ነው[4]። ሐዋርያው ሃሳቡን የገለጠው ፍጹም በማያሻማና ጠንካራ በሆነ መልኩ ነው፦

> *"እንግዲህ የቤተክርስቲያን ምእመናን በአንድነት በተሰበሰቡበት ፣ ሁሉም በልሳን በመናገር ላይ ሳሉ ፣ እንግዶች ወይም የማያምኑ ሰዎች ወደጉባኤው ቢገቡ ፣ አብደዋል አይሉምን?" (14 ፡ 23)*

ሐዋርያው ይህን በመሰለ ጽናት የማያምኑ ሰዎች ባሉበት ስብሰባ ልሳን ያለትርጉም በከፍተኛ ድምፅ እንዳይነገር ካስጠነቀቀ በኋላ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ይህን ሃሳቡን መልሶ ሊሽረው አይችልም።

አንዳንዶች ፣ "ስለዚህ በልሳን መናገር ለማያምኑ የሚሆን ምልክት እንጂ ለሚያምኑ አይደለም..." (ቁ 22) የሚለውን ቃል ጠቅሰው ፣ የማያምኑ ሰዎችን ወደክርስቶስ ለማምጣት እንዲያውም አብዝተን በልሳን መናገር ይገባናል ይላሉ። የዚህ ጥቅስ ፍቺ ይህ ማለት ከሆነ ፣ እንግዲያውስ ሐዋርያው በመልዕክቱ በአንዱ ምዕራፍ ውስጥ ራሱን በከባድ ሁኔታ ተቃርኗል ማለት ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ቅራኔ በራሱ ሃሳብ ላይ ሊያመጣ የሚችል እብድ ሰው እንጂ ጤናማ ሊሆን አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ መልኩ ራሱን በራሱ ሊቃረን ይችላል የሚል አቋም ከያዝን እንግዲያው ይህ መጽሐፍ ሥልጣን ያለው የእግዚአብሔር ቃል ያለበት መጽሐፍ ሊሆን አይችልም ፣ ግራ ስለሚያጋባም መነበብ የለበትም ማለት ነው። ይህን የመሰለ አደገኛ ስህተት ውስጥ እንዳንገባ የሚረዳን "መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ አይቃረንም" የሚለውን ጤናማ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት መርህ ስናከብር ነው[5]።

የጠቀስናቸው ሁለት ክፍሎች ያላቸው የሚመስለውን ተቃርኖ መፍታት የሚቻለው ፣ በቅድሚያ አሻሚ ባልሆነ መልኩ የተቀመጠው ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ ሊያስተላልፈው የፈለገው ሃሳብ ነው ብሎ በመቀበል ነው። ቀጥሎ መወሰድ ያለበት እርምጃ ግልጽ ያልሆነውን ጥቅስ ፍቺ ለማግኘት መሞከር ነው። ለዚህ የሚረዳን የአፈታት መርህ "ግልጽ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅደስ ክፍል ፣ ግልጽ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይፈታል" የሚለው ነው[6]። 1ኛ ቆሮንቶስ 14 ቁጥር 21 - 22ን በዚህ መንገድ ለመፍታት አስቸጋሪ አይደለም። ቁጥር 21 የተጠቀሰው ከኢሳይያስ ምዕራፍ 28 ፡ 11 - 12 ካለው ክፍል ነው። ይህ ጥቅስ የሚገኝበትን ምዕራፍ በሙሉ ስናነበው የተጠቀሰው ቃል በእስራኤል ላይ የተነገረ የፍርድ ቃል እንጂ የደኅንነት የተስፋ ቃል እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ነቢዩ በቋንቋቸው የተናገረውን ቀላልና ግልጽ መመሪያ ተቀብለው ከመታዘዝ ይልቅ የፌዝ ምላሽ በመስጠታቸው (ኢሳ 28 ፡ 9 - 10) ፣ በባዕድ ልሳን በእንግዳ ቋንቋ ሊናገራቸው እግዚአብሔር ወሰነ። ይህ የፍርድ ትንቢት የተፈጸመው በአሦራዊያን ወረራ አማካይነት እንደሆነ ይታመናል። በቋንቋቸው የተነገራቸውን መስማት እንቢ ያሉት እስራኤላዊያን በማያውቁት ቋንቋ የአሦራዊያንን ቁጣ መስማት ግዴታ ሆነባቸው።

ከፍ ብዬ እንደጠቀስሁት ፣ በኢሳይያስ ዘመን አሉታዊ ትርጉም የነበረው ቃል በሐዋርያት ዘመን ወይም በእኛ ዘመን አዎንታዊ ትርጉም ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ እኛ የተጠራነው ለማያምኑ ሰዎች ወንጌልን እንድንሰብክ እንጂ የፍርድን ቃል እንድናስተላልፍባቸው ስላልሆነ ፣ የማያምኑ ሰዎች ባሉበት ጉባኤ ጮክ ብለን በልሳን መናገራችን ተገቢ አይደለም ማለት ነው። እንግዲህ ሐዋርያው ጳውሎስ ከኢሳይያስ ይህን ቃል የጠቀሰው የቆሮንቶስ ሰዎች በማያምኑ ሰዎች ጆሮ በልሳን ከመናገር እንዲታቀቡ ለማስጠንቀቅ እንጂ እንዲናገሩ ለማበረታታት አልነበረም።



አንዳንድ ክርስቲያኖችም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 የተጻፈውን የበዓለ ሃምሳውን ልምምድ በመጥቀስ ተርጓሚ ባይኖርም ያላመኑ ሰዎች ባሉበት በልሳን መናገር መከልከል የለበትም ብለው ይከራከራሉ። እዚህ ላይ ማጤን የሚያስፈልገን የበዓለ ሃምሳው ሁኔታና የሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ መልዕክት የሚመለከተው ሁኔታ የማይመሳሰሉ መሆናቸውን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸውን ተሞክሮዎች ለዘመናችን ሁኔታ አዛምደን ልንጠቀም ከፈለግን በዚያ ዘመን የነበረው ሁኔታ ከእኛ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልገናል። ለምሳሌ ፣ አዲስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ሲጸለይላቸው ፣ መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይል በላያቸው ቢወርድና ሁላቸውም ድምፅ አውጥተው በተለያዩ ልሳኖች መናገር ቢጀምሩ ፣ ሁኔታውም በአካባቢው የሚገኙ የማያምኑ ሰዎችን ሃሳብ የሚስብ ሆኖ ቢገኝ ፣ ከኢየሩሳሌሙ የበዓለ ሃምሳ ክስተት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል። በዚህ ሂደት መንፈስ ቅዱስ የጥንቱን ተሞክሮ አሁን እየደገመው ከሆነ ዘንዳ ፣ በዚያን ጊዜ እንደሆነው ሁሉ ፣ በመገረም የሚያዳምጡት የማያምኑ ሰዎች በየቋንቋቸው እግዚአብሔር ሲመሰገን ይሰማሉ ብለን እንጠብቃለን። በዚህ ሁኔታ የማያምኑ ሰዎች ልሳን ቢሰሙ አይሰናከሉም። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልዕክት የተመለከተው ጉዳይ በመደበኛ የአምልኮ ፕሮግራም የሚሆነው የልሳን አጠቃቀም በመሆኑ ፣ ከበዓለ-ሃምሳው ሁኔታ ፈጽሞ የተለየ ነው። በዚህኛው ሁኔታ በልሳን አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገ የማያምኑ ሰዎች ይሰናከላሉ።

## ሐ) የልሳን ስጦታ አጠቃቀምን ሥርዓት በማስያዝ ረገድ የመሪዎች ሚና

ይህችን ጽሑፍ ሳቀርብ ያለኝ ተስፋ ፣ ያነሳኋቸው ሃሳቦች ለአንባቢው ግልጽ ስለሚሆኑ ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች በየበኩላቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋሉ የሚል ነው። ሆኖም ግን በየቤተ ክርስቲያኑ ያሉ ምዕመናን በተለያየ የእምነት ፣ የብስለትና የአመለካከት ደረጃ ላይ ስለሚሆኑ ፣ በሁሉ ዘንድ አንድ ወጥ የሆነ አቀባበል ይኖራል ብሎ መጠበቅ ስህተት ይሆናል። ስለዚህም የእግዚአበሔር ቃል መመሪያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረጉ ኃላፊነት በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና እረኞች ጫንቃ ላይ ይሆናል። መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ያስፈለጉበት አንዱ ምክኒያት ይኸው ነው።

አስተማማኝ በሆነ መንገድ ሥርዓት ለማስያዝ ከተፈለገ በቅድሚያ መደረግ ያለበት ለአገልጋዮችና ለአባላት ሁሉ ሚዛናዊ የሆነ ትምህርት መስጠት ነው። ከትምህርቱ ጋር በቂ የሆነ የውይይት ጊዜ በመስጠት በአባላት አእምሮ ውስጥ ያሉ ጥያቄዎችን መመለስና የተዛቡ አመለካከቶችን ማስተካከል ያስፈልጋል። በአብዛኛዎቹ አባላት ዘንድ ተመሳሳይ መረዳት ላይ ከተደረሰ በኋላ ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችን በጽሑፍ አስቀምጦ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ

ተግባራዊ እንዲሆኑ የቅርብ ክትትል ማድረግ ይቻላል። ከክትትል አኳያ የበለጠ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የፕሮግራም መሪዎችና ሰባኪዎች ናቸው። እነዚህ አገልጋዮች ድምፅ ማጉያ ስለሚጠቀሙ የሚደርሰው ጥፋት እጥፍ ድርብ ነው። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ድምፅ ማጉያው በቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከአዳራሹ ውጪም ይተከላል። በአንድ ወቅት በአንድ የክፍለ ሃገር ከተማ ለአገልግሎት ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን በእግሬ እየሄድሁ ሳለሁ ገና በከተማው ዋና መንገድ ላይ እያለሁ ከሜጋፎን የሚኈነደነደው የልሳን ድምፅ አካባቢውን ሲያናውጥ ሰምቼ እጅግ ተሸማቀቅሁ። የሐዋርያው ጳውሎስን ትምህርት ለዚህ ሁኔታ ብንተረጉመው ፣ በስብሰባው አዳራሽ የሚገኙትን የማያምኑ ሰዎች ማሰናከል ብቻ ሳይሆን ፣ ገና በሩቅ ያሉትንም "አትድረሱብን!" የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ይሆናል።

ሌላው በትላልቅ ከተሞችም ሆነ በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በተደጋጋሚ የታዘብሁት ፣ "ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጌታ በሰጣችሁ ልሳን ጸልዩ" እያሉ ፕሮግራም መሪዎች ለሚያመልከው ሕዝብ የሚሰጡት መመሪያ ነው። ይህ ዓይነቱ መመሪያ ፣ የሚጠቀሙበት" ቃል እንኳን ሳይቀየር ከመሃል ሃገር እስከጠረፍ ድረስ የተንሰራፋ መሆኑ ራሱ አስደናቂ ክስተት ነው። የእኔ ግምት ፣ የነገሩ ምንጭ በዋና ከተማ ያሉ ሰፋፊ አጥቢያዎች መድረክ ይሆንና ከየክፍለ-ሃገሩ ለጉዳዩ የሚመጡ አገልጋዮች አሠራሩን ሳይመረምሩ በመቀበል በየቤተ ክርስቲያናቸው ተግባራዊ እያደረጉት ይመስለኛል። ከፍ ባሉት ክፍሎች በዝርዝር እንደተመለከትነው "ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በልሳን ጸልዩ" የሚለው መመሪያ የሐዋርያው ጳውሎስን ትምህርት መቶ በመቶ የሚቃረን ነው። ስለዚህም ያላመኑ ሰዎችን በወንጌል ለመማረክ ሃሳብ ባላት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ፕሮግራም ወቅት ይህ ዓይነቱ ቃሉን የሚቃረን አሠራር መፈቀድ የለበትም።

እንደዚሁም አንዳንድ ሰባኪዎች ጉባኤው በሚሰማው ቋንቋ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልዕክት ማስተላለፍ ሲገባቸው ፣ ስሜታቸው ጋል ባለ ቁጥር በድምፅ ማጉያ በልሳን ይናገራሉ። በስብከት መካከል ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ አስቸኳይ መልዕክት በልሳን ተናግረው ትርጉሙንም አብረው የሚሰጡ ቢሆን ተቀባይነት በኖረው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህም ሁኔታ የሚናገረን አለው፦

> *"ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተማር ፣ ዐስር ሺህ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ብናገር ይሻላል" (1ኛ ቆሮ 14 ፡ 18 - 19)።*

ከዚህ አገላለጽ እንደምንረዳው ፣ በአደባባይ በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ግፊት ሳይሆን የግለሰቡ ውሳኔ መሆኑን ነው። ሐዋርያው ከማንም የበለጠ በልሳን የመናገር ልምምድ ቢኖረውም በጉባኤ ሲሰብክ ራሱን ገዝቶ ሰው በሚገባው



ቋንቋ ይናገር ነበር። ዛሬም እንደጳውሎስ እንዳናደርግ የሚከለክለን ምንም ነገር የለም። በፕሮገራም መሪዎች እንደገመትሁት ሁሉ በሰባኪዎችም አካባቢ የሌሎችን "እውቅ" ሰባኪዎች ልምድ ያለጥንቃቄ የመቅሰሙ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በተለይም በውጪ ሃገር ትላልቅ ጉባኤዎች የሚሰብኩ አገልጋዮች ስብከት በቪዲዮ በስፋት መሠራጨቱ ለዚህ ክስተት አስተዋፅዖ የሚያደርግ ይመስለኛል። እዚህ ላይ ለማስገንዘብ የምወደው በውጪ ሃገር ያሉ ትላልቅ ጉባኤዎችና የእኛ ቤተ ክርስቲያኖች የአምልኮ ፕሮግራሞች ተመሳሳይ አለመሆናቸውን ነው። በቪዲዮ የሚታዩት የውጪ አገር ጉባኤዎች በአብዛኛው ወይም ሙሉ በሙሉ ለየት ያለ ትምህርት ለመስማት ፣ ወይም የአካል ፈውስ ለማግኘት ፣ ወይም ብልጥግና ለማግኘት ወዘተርፈ የሚሰበሰቡ አማኞች ናቸው። እነዚህን በሚመስሉ ጉባኤዎች ያለገደብ በልሳን መናገር ማንንም ላያሰናክል ይችላል።

የእኛ አገር ቤተ ክርስቲያኖች ግን በአምልኮ ፕሮገራም ወቅት የማያምኑ ሰዎችን እንዲያስተናግዱ ይጠበቃል። የ1986 ዓ.ም የሕዝብ ቆጠራ[7] ውጤት እንዳሳየው "ፕሮቴስታንት ነኝ" የሚለው ሕዝብ ብዛት 10.2% ብቻ ሆኖ ነው የተገኘው። ይህ ስሌት በከተሞች ዝቅተኛ ደረጃ ይዞ 5.4% ላይ ነው የተገኘው። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ደግሞ ዳግም ተወልዶ ክርስቶስን በትክክል የሚያመልከውን መለየት ቢቻል ስሌቱ ዝቅተኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ያለንበት እውነታ ይህ ስለሆነ በዙሪያችን በገፍ ያሉትን የማያምኑ ሰዎች በወንጌል ለመማረክ ያላሰለሰ ጥረትና ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታ ይሆንብናል። ይህን ሁሉ ሕዝብ በውጪ ትተን በውስጥ ያለን ሰዎች የራሳችንን ስሜት ለማርካት ብቻ አምልኮ ብናደርግ ፣ ከወንጌል ሥርጭት አኳያ ከፍተኛ ኪሳራ ከመሆኑም በላይ ፣ እግዚአብሔርን እናሳዝናለን። አንዳንዶች "በልሳን ያለገደብ እየተናገርንስ ሰዎች ይድኑ የለም ወይ?" ብለዋል። አዎን ፣ የእኛን አለማስተዋል ተቋቁመው ወደጌታ ስለመጡት ጥቂቶቹ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ነገር ግን ያለሥርዓት የሚነገር ልሳንና ጩኸት ከቤተክርስቲያን አካባቢ ያራቃቸው ሰዎች ብዛት ከዳኑት ጋር ሲወዳደር ሃምሳና መቶ እጥፍ ሊሆን ይቻላል። የመንግሥተ-ሰማያት ደጅ ስለተዘጋባቸው ስለነዚህ አእላፋትስ ማነው ተጠያቂ? ውድ ወገኖቼ ፣ ጠንካራ በሆኑ ቃላት እንድጽፍ የሚያስገድደኝ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ላይ እየተፈጠረ ያለው ይህን የመሰለው አደጋ ነው።

በስብከት ወቅት ልሳን ያለአግባብ እንዳይነገር ለማድረግም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ስር-ነቀል በሆነ መልኩ ማደራጀት ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ደረጃ የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋይ የሆኑ ሰባኪዎች ልሳንን በሚመለከት ሥርዓት እንዲይዙ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ትምህርትና ውይይት አድርጎ ቋሚ መመሪያ ማውጣት ያስፈልጋል። በሁለተኛ ደረጃ ፣ አገልጋይ ከውጪ ሲጋበዝ ፣ ቀጠሮውን ከመያዙ በፊት ልሳንን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያላት አቋም በግልጽ ሊነገረው ይገባል። የሚስማማው ከሆነ ቀጠሮ ይይዛል ፣ ካልተስማማው ደግሞ ሊተወው ይችላል። እዚህ ላይ እግረ-መንገዴን ማንሳት የምፈልገው ፣

ከመጠን በላይ እየተስፋፋ ያለው አገልጋዮችን ከውጪ አብዝቶ የመጋበዙ ልማድ እንዲታሰብበት ነው። በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መድረክ በአብዛኛው ዕሁዶች ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የተጋበዙ ሰዎች የሚሰብኩ ከሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱ የራሷ አገልጋዮች ሥራቸው ምንድነው የሚሆነው? እግዚአብሔር ለእያንዳንዷ አጥቢያ የስብከትና የማስተማር ጸጋ አይሰጥምን? ለምዕመኑ ትክክለኛ ሸክም ኖሮት መፍትሔ የሚሆን መልዕክትን ከእግዚአብሔር ለመቀበል የቤቱ ሰው ይሻላል ወይስ ከውጪ የሚመጣ እንግዳ? የቤቱ አገልጋዮች በራሳቸው ሕዝብ መካከል የአገልግሎት መድረክ አዘውትሮ ካልተሰጣቸው ጸጋቸው እንዴትስ ሊያድግ ይችላል? ለአጥቢያይቱ የተሰጠን ጸጋ ከመጠቀምና አገልጋዮቿን ለማሳደግ ከማሰብ አኳያና ፣ ቤተክርስቲያን ለተለያዩ ግድፈቶች እንዳትጋለጥ ለመከላከል ፣ አዘውትሮ የውጪ አገልጋዮችን የመጋበዝን አጉል ልማድ መተው እንደሚያስፈልግ አምናለሁ። ይህ እርምጃ ሲወሰድ ደግሞ በአጥቢያይቱ መድረክ ላይ አንድ አገልጋይ ብቻ ከወር እስከ ወር ያገልግል ማለት አይደለም። በቤተ ክርስተያኒቱ ውስጥ ያሉት የማስተማርና የመስበክ ጸጋ የተሰጣቸው በሳል አገልጋዮች በፈረቃ ማገልገላቸው አስፈላጊ ነው። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ይህን ይመስል ነበር። ጳውሎስና በርናባስ አብረዋቸው ሳሉ አምስት አስተማሪዎችና ነቢያት በቤተ ክርስቲያኒቱ ነበሩ (ሐሥ 13 ፡ 1) ፣ ጳውሎስና በርናባስ ለዓለም-አቀፍ አገልግሎት ከተለዩ በኋላ የቃሉ አገልጋዮች ቁጥር ከመቀነስ ይልቅ በብዙ ጨምሯል (ሐሥ 15 ፡ 35)።

## መ) የትንቢት ስጦታ አጠቃቀም

የልሳን ስጦታ ያነጋገረንን ያህል የትንቢት ስጦታ አያነጋግረንም። የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ችግር ልሳንን ከሌሎች የጸጋ ስጦታዎች የማስበለጥና ከልክ በላይ የመጠቀም ሁኔታ ነበር ፣ ስለዚህም ሐዋርያው የበዙትን ቃላት የተጠቀመው ይህን ሁኔታ ለማረም ነበር። እኛም እያጋጠመን ያለው ችግር ተመሳሳይ በመሆኑ ጊዜ ወስጄ የተረዳሁትን ጽፌአለሁ። የትንቢት ስጦታን በተመለከተ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ፣ የስጦታውን ጠቀሜታ በውል ካለመረዳት የተነሳ በተገቢው መጠን አለመጠቀማቸው ነበረ። የእኛ ቤተ ክርስቲያኖች ችግር ግን ከዚህ ይለያል። የትንቢትን ጠቀሜታ ያለመገንዘብ ችግር አይደለም። ትንቢቶች በብስለትና ሥርዓትን በመከተል ካለመነገራቸው የተነሳ የሚከሰቱትን ውዝግቦች ከመፍራት የተነሳ በደፈናው ስጦታውን የማፈን ችግር ነው። በዚህ ክፍል የሚቀርበው ፍሬ ሃሳብ ፣ ትንቢቶች ጤናማ በሆነ መልኩ የሚነገሩበትን አሠራር በማስገንዘብ ፣ በተረጋጋ ሁኔታ ትንቢቶች በጉባኤ አዘውትረው የሚነገሩበትን መንገድ ለማሳየት ይሆናል።

በያዝነው በቆሮንቶስ መልዕክት ትምህርት መሠረት የትንቢት ስጦታ ዋናው አገልግሎት ቤተክርስቲያንን ለማነጽ ፣ ለማበረታታትና ለማጽናናት ነው[8]። የትንቢት መልእክት ሲነገር የማያምኑ ሰዎች ቢኖሩም ፣ በቋንቋቸው እየተነገረ ስለሆነ አይሰናከሉበትም። የመልዕክቱ ይዘት በአብዛኛው



የእግዚአብሔርን ታላቅነት ፣ ፍቅሩን፣ ምሕረቱን የሚያውጅና ፣ ሰዎች በጥንቃቄ ሕይወታቸውን እንዲመሩ የሚያሳስብ ስለሚሆን ፣ የማያምኑ ሰዎችንም ይናገራቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የማያምነውን ሰው በቀጥታ የሚመለከተው ቃል በትንቢት ስጦታ አማካኝነት ተገልጦ ወደ ንስሐ ሊመራው ይችላል[9]።

የትንቢት ስጦታ በጣም ጠቃሚ ስጦታ ቢሆንም እንኳን ለአንድ የአምልኮ ፕሮግራም ብቻውን በቂ አይሆንም። ሕዝቡ የተሟላ አገልግሎት እንዲያገኝ የተለያዩ ጸጋዎች ተግባራዊ የሚሆኑበት አመቺ መርሐ-ግብር መንደፍ አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ መሠረተ ሃሳቡን እንደሚከተለው አስቀምጦታል።

> *"ወንድሞች ሆይ ፣ እንግዲህ ምን እንበል? በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳንዱ መዝሙር አለው ፣ ትምህርት አለው ፣ መግለጥ አለው ፣ በልሳን መናገር አለው ፣ መተርጎም አለው። ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ ይሁን። በልሳን የሚናገር ቢኖር ፣ ሁለት ወይም ሦስት በየተራ ይናገሩ ፣ ሌላው ደግሞ ይተርጉም ፣ ... ሁለት ወይም ሦስት ነቢያት ይናገሩ ሌሎቹ ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ ይመዝኑ" (ቁ.26-27 ፣ ... 29)።*

በአብዛኞቹ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች የአምልኮ ፕሮግራም ፣ ለመዝሙር ፣ ለስብከት ፣ ለመባ ፣ ለማስታወቂያ ፣ ለጸሎት የተመደበ ጊዜ ይሰጣል። ስለዚህም እነዚህ አገልግሎቶች በሰዓታቸው ይፈጸማሉ። ለሚተረጎም ልሳንና ለትንቢት ግን የተወሰነ ጊዜ መመደብ የተለመደ አይደለም። የትንቢት ስጦታ ያላቸው አንዳንድ አገልጋዮች አመቺ ይሆናል ብለው በገመቱት ጊዜ መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ሲሞክሩ ከመድረክ የሚከለከሉበትም ጊዜ አለ። እንደዚህ ያለው አሠራር ተናጋሪውን ከማስደንገጥም አልፎ አባላቱን ሁሉ ቅር የሚያሰኝ ይሆናል። በእምነት ገና ያልጸኑት ደግሞ በእግዚአብሔር ስም የሚናገር ሰው በዚህ መልኩ ሲታገድ ፣ መድረኩን የያዙት ሰዎች እግዚአብሔርን የተዳፈሩት መስሏቸው ሊሰናከሉም ይችላሉ።

የጌታን ቃል በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ብናደርገው ግን ቤተ ክርስቲያን ከመተራመስ ትተርፋለች። ለሌሎች አገልግሎቶች ጊዜ እንደሚመደብ ሁሉ ለትንቢትም ጊዜ መመደብ ያስፈልጋል ፣ ይቻላልም። የሚተረጎም ልሳንም አገልግሎቱ እንደትንቢት ስለሆነ ፣ ስለትንቢት የምጽፈውን ለሚተረጎም ልሳንም ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል። ስለዚህ ከዚህ በኋላ አላነሳውም። ሐዋርያው እንዳስተማረው ፣ በአንድ የአምልኮ ፕሮግራም ወቅት ትንቢት እንዲናገሩ የሚፈቀድላቸው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ብቻ ስለሚሆኑ በጠቅላላው የሚወስደው ጊዜ ብዙ አይሆንም። በተለይ ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ትንቢት ተገቢው ሥልጠና በተሰጣቸው ሰዎች ሲነገር የሚነገሩት ቃላት ብዛት ምጥን ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ሕዝቡን በወቅቱ ካስተማሩና የአፈጻጸም መመሪያዎችን በተደጋጋሚ በቃልና በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ

በሚለጠፍ ግልጽ ጽሑፍ ካስረዱ ፣ የትንቢት አገልግሎት በጥሩ ስነ-ሥርዓት እየቀረበ ሕዝቡ የበረከት ተጠቃሚ የማይሆንበት ምንም ምክኒያት የለም። በሲንግጋፖር ከተማ ባለች በአንድ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በምትጠቀም የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ውብ የሆነ ስነ-ሥርዓት አይቻለሁ። የእለቱ ስብከት ከቀረበ በኋላ በተመደበው ሰዓት ፕሮግራም መሪው ትንቢት ወይም ሌላ የመግለጥ ስጦታ ያላቸው ሰዎች መልዕክታቸውን እንዲያቀርቡ ይጋብዛል። በአዳራሹ ውስጥ ያለው 1500 ያህል ሕዝብ በፍጹም ጸጥታ እየጠበቀ መልዕክት ያለው ሰው ወደ መድረኩ ወጥቶ ፣ ድምፅ ማጉያውን እየተጠቀመ ፣ ያለምንም መርበትበት በተረጋጋ ስሜትና ጥርት ባለ ድምፅ ፣ ትንቢትም ቢሆን ፣ ራዕይ ቢሆን ይናገራል። ሕዝቡ ከመስማት በስተቀር መልዕክቱ ተጀምሮ እስከሚጨረስ ድረስ ፣ ካለቀም በኋላ ፣ ድምፅ አያሰማም። ሁለት ተከታታይ ዕሁዶች ተካፍያለሁ ፣ ስነ-ሥርዓቱ እንደተጠበቀ ነበር። በመሪዎቹም ፣ በሕዝቡም በኩል ስላየሁት ስለዚህ ማስተዋልና አብሬአቸውም ስለጠጣሁት የጠለለ የበረከት ምንጭ እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ ነው ያመሰገንሁት። አልፎ አልፎ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች የትንቢት መልዕክት ያላቸው ሰዎች የመልዕክቱን ይዘት በቅድሚያ ለቤተክርስቲያን መሪዎች ገልጸው ከተፈቀደላቸው ለጉባኤው እንዲናገሩ ይደረጋሉ። ይህ ዓይነቱ አሠራር በሜዳ ላይ ለሚደረግ የጅማ ስብሰባ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ትንቢት ለመናገር የሚፈልጉ ሰዎች ማንነት በውል ስለማይታወቅ ፣ እንደዚሁም በሜዳ የሚሰበሰበው ሕዝብ በበጎም በአፍራሽም ዓላማ የተሰበሰበ ስለሚሆን ፣ ከስብከት ጀምሮ በማንኛውም መልኩ በሚተላለፉ መልዕክቶችና በሚነገሩ ማስታወቂያዎች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ ግን በዚህ መልኩ መሥራት አስፈላጊ አይደለም ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ መሪዎች፣ በተለይም እረኛው ፣ አባላቱ ምን ዓይነት ጸጋ እንዳላቸውና እንደሌላቸው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። በመልካም መንፈሳዊ ሕይወት የሚመላለስ የትንቢት ስጦታ ያለው አገልጋይ መልዕክት በመጣለት ቁጥር በገዛ ቤተ ክርስቲያኑ ይዘቱን ለመሪዎች እያስረዳ ፈቃድ መጠየቁ አግባብ አይደለም። የምናውቀውን ነቢይ በዚህ መልኩ እንቆጣጠር ካልን ፣ ሰባኪም መድረክ ከመያዙ በፊት የስብከቱን አስተዋፅዖ ለመሪዎች አስነብቦ ፈቃድ ማግኘት አለበት ማለት ሊኖርብን ነው። ትንቢት እንዳይነገር የመከልከል ያህል ባይከፋም ይህም ዓይነቱ አሠራር "የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ ፣ ትንቢትን አትናቁ" (1ኛ ተሰ 5 ፡ 19 - 20) የሚለውን የቃሉን ትምህርት ይጋፋል። የትኛውንም የጸጋ ስጦታ መገፍተር ለቤተ ክረስቲያን አይበጅም። ስጦታዎቸ አንድ በአንድ እየተዳፈኑ ራቁት መቅረት ይመጣልና! ይህን ስል ትንቢት መመርመር አያስፈልገውም ለማለት አይደለም። ትንቢት በትጋት መመርመር ያስፈልገዋል። ለዚህ ግን አመርቂ የሆነ የቃሉ መመሪያ አለን ፣ የሚከተሉት አንቀጾች እርሱን ያሳዩናል።



## ሠ) ትንቢትን በመመዘንና ሥርዓትን በማስፈን ረገድ የመሪዎች ሚና

ትንቢትን የመመዘን ወይም የመመርመር አስፈላጊነቱ በአዲስ ኪዳን ትምህርት ግልጽ ነው[10]። ትንቢትን መመዘን አስፈላጊ የሚሆንበት ሦስት መሠረታዊ ምክኒያቶች አሉ። አንዱ የትንቢት መልዕክት አመጣጡ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የትንቢት መልዕክት ለአገልጋዩ የሚመጣው በመንፈስ ውስጥ በሚታወቅ የእግዚአበሔር ሃሳብ ነው። በቂ ልምድ እስኪገኝ ድረስ ከዚህ ዓይነቱ መረጃ ተነስቶ ጥርት ያለ መልዕክት ማስተላለፍ ቀላል አይደለም። ጽሑፍ በራዕይ እያየ ወይም መልዕክቱን ቃል በቃል በድምፅ እየሰማ ፣ ነቢዩ ተቀብሎ የሚናገርባቸው ሁኔታዎች የተለመዱ አይደሉም። ሁለተኛው ምክኒያት የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው በክርስትና ሕይወቱ ያልበሰለና ፣ ጠለቅ ያለ የቃሉ እውቀት የሌለው ሰው ሊሆን ስለሚችል ነው። ይህ የሚጠበቅ ነው ፣ ምክኒያቱም መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታን የሚሰጠው የሕይወትን ብስለት እያየ አይደለም። ይህን ሃሳብ በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ ገልጬዋለሁ። ሦስተኛው ምክኒያት መንፈስ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ክፉ መንፈስም የትንቢት መልዕክት ማቀበል ስለሚችል ነው (1ኛ ዮሐ 4 ፡ 1)።

የጠቀስኳቸው ምክኒያቶች ` ግልጽ ምክኒያቶች ስለሆኑ ፣ የእግዚአብሔርም ቃል በግልጽ ስለሚመራን ፣ የትንቢት መመዘን የቤተክርስቲያኒቱን አባላት አገልጋዮች ፣ እንዲሁም መሪዎች ደስ ሊያሰኛቸው ይገባል። አባላት ለተዛነፈና ለተሳሳተ የትንቢት መልዕክት ከመጋለጥ ይተርፋሉ። የቃሉን መመሪያ በተከተለ መንገድና ፣ አግባብነት ባላቸው አገልጋዮች ትንቢታቸው ስለሚመረመር ፣ ነቢያት ሸክም ይቀልላቸዋል። "ተሳስቼ ይሆን ወይ?" የሚለው ስጋት አያስጨንቃቸውም። በብዙዎች ሰዎች ተመዝኖ ያለፈው ጤናማ ነው ፣ እርምት የተደረገበት ደግሞ ችግር ያለበት ነው። ጤናማ የሆነውና ችግር ያለበት በዚህ መልኩ ሲለይ አስተዋይ ነቢይ ትምህርት ይማርበታል። ትህትናንም እየተለማመደ ስለሆነ እግዚአብሔር ጸጋን ስለሚጨምርለት በአገልግሎቱ እያደገ ይሄዳል። የቤተክርስቲያን መሪዎችም ትንቢቶች እንዲመረመሩና ሁሉ በአግባብና በሥርዓት እንዲመራ በማድረግ ኃለፊነታቸውን ስለሚወጡ የሕሊና እርካታ ይኖራቸዋል። ይህ ዓይነቱ ግልጽ አሠራር በቤተ ክርስቲያን ሲሰፍን የጸጋ ስጦታዎች በበለጠ ነፃነት ይገለጣሉ። በቅርቡ ጸጋን የተቀበሉ ገና ያልበሰሉ አባላት እንኳን ዋስትና ስለሚሰማቸው ጸጋቸውን መለማመድ አይፈሩም። መሪዎችም ከበቂ ትምህርት ጋር ጀማሪዎች ጸጋቸውን እንዲገልጡ ማደፋፈራቸው ተገቢ ነው። በእኔ እምነት ፣ በቅንነትና በንፁህ ልብ የሚናገሩ ጀማሪ ነቢያት በመልዕክቱ ሃሳብ ላይ የጎላ ስህተት አይፈጥሩም፣ መንፈሳዊ ቃላትን ተጠቅመው የተስተካከሉ ዐርፍተ-ነገሮችን መናገር ይቸግራቸው ይሆናል እንጂ። የበለጠ ጎጂ የትንቢት ይዘት መዛባት የሚከሰተው ልምድ ያላቸው ነቢያት በተለያዩ ምክኒያቶች የተበላሸ ሕይወት ውስጥ ገብተው ሳሉ የትንቢት መልዕክት ለማስተላለፍ ሲሞክሩ ነው[11]።

ትንቢትን የመመዘን አስፈላጊነቱን ይህን ያህል ከገለጽሁ ፣ ከዚህ በኋላ የሚቀረኝ ዋና ፍሬ ሃሳብ ፣ ትንቢቶች የሚመዘኑበትን ዘዴ ማመልከቱ ነው። ለመከታተል እንዲያመች ሃሳቦቹን ነጥብ በነጥብ ማስቀመጡ ይቀላል፦

## ➢ ትንቢት በሌሎች ነቢያት ይመዘናል (1ኛ ቆሮ 14 : 29 - 31)

ነቢያት ትንቢትን የመመዘን ድርሻ መውሰዳቸው በሁለት ምክኒያቶች ተፈላጊ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በአገልግሎቱ ልምድ ስላላቸው ፣ መልዕክት እያቀረበ ያለው ነቢይ ስህተት ሲያጋጥመው በቶሎ ሊታወቃቸው ይችላል። ተቀምጠው የሚያዳምጡት ነቢያት ለራሳቸው በውጥረት ውስጥ ስለማይሆኑ መልዕክቱን ለመመዘን ይቀላቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ ፣ እየተነገረ ያለውን ትንቢት የሚመስል ይዘት ያለው መልዕክት ሌሎቹም ነቢያት ሊቀበሉ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ደግሞ መድረክ የተሰጠው ነቢይ በሆነ ምክኒያት በመልዕክቱ ላይ ልዩ ሃሳብ ቢጨምርበት ጭማሪውን መለየት ይቻላል።

እየተነገረ ባለው ትንቢት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳ ጉልህ ስህተት ቢገኝበትና ስህተቱ እንዲታረም መንፈስ ቅዱስ ቢያመለክት ከተቀመጡት መካከል አንዱ ነቢይ ተነስቶ የተስተካከለውን መልዕክት ማቅረብ ይኖርበታል (ቁ 30)። ይህ ሲሆን ቀደም ሲል ይናገር የነበረው ነቢይ ዝም ማለት አለበት። የነቢያት መንፈስ ለነቢያት ስለሚታዘዝ የቀደመው ነቢይ መልዕክቱን ለማቋረጥ አይቸገርም።

## ➢ ትንቢት በተጻፈው በእግዚአብሔር ቃል ይመዘናል
(1ኛ ጴጥ 4 : 10 - 11 ፣ 2ኛ ጴጥ 4 : 16 - 21 ፣ ዮሐ 14 : 26)

የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ እርስ በእርሱ እንደማይቀዋወም ሁሉ ፣ በትንቢት ስጦታ የሚነገረውም ቃል የአንዱ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚናገረው ቃል ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ሊቃረን አይችልም። እግዚአብሔር ራሱን በራሱ ስለማይቃረን ከቃሉ ጋር የሚቃረን የትንቢት ቃል ከሥጋ ወይም ከክፉ መንፈስ የመነጨ ነው ማለት ነው። ክርስትናን ከስህተት ትምህርቶች የሚለየውና ፍጹም አስተማማኝ የሚያደርገው ይህ እውነት ነው። የስህተት ትምህርቶች በተለያዩ ጊዜያት በሚነሱ የራሳቸው ነቢያት በኩል በሚመጡ መገለጦች ይታረማሉ። የክርስትና እምነት ግን በጽሑፍ መስፈር ያለበት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው በጻፉ መልዕክተኞች በ66 መጻሕፍት ውስጥ ተካትቶ ተደምድሟል። በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚገለጥ መልዕክት ከተጻፈው ቃል ጋር ፍጹም እንዲስማማ ይጠበቃል። ይህ ካልሆነ ግን በአዳዲስ መልዕክቶች እየፈረሰ እምነቱ መሠረት የሌለው ይሆናል።

የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቅመው ትንቢትን መመዘን የሚጠበቅባቸው መሪዎችና በሳል አገልጋዮች ናቸው። ለዚህ ኃላፊነት የተዘጋጁ



እንዲሆኑ መሪ አገልጋዮች አዘውትረው የእግዚአብሔርን ቃል በስፋት ማጥናታቸው አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የመከረው ይህንኑ ነው።

> *"እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።"*
> 2ኛ ጢሞ 2 : 15

የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል የሚቃረን ትንቢት ሲነገር ፣ እንደ ቅራኔው አሳሳቢነት ትንቢቱ ባስቸኳይ እንዲቋረጥ አድርገው ማስተካከያውን ሊሰጡ ፣ አለዚያም መልዕክቱ ከተላለፈ በኋላ ነቢዩን ሊመክሩ ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ማስተካከያውን ለጉባኤው ሊነግሩ ይችላሉ።

## ➢ የመልዕክቱን አጠቃላይ ይዘት በመገምገም ትንቢት ይመዘናል

የጸጋ ስጦታ የሆነው ትንቢት ዓላማ ቅዱሳንን ለማነጽ ፣ ለማበረታታትና ለማጽናናት መሆኑን ቃሉ ይናገራል (1ኛ ቆሮ 14 : 3)። ከዚህ መንፈስ ውጪ ሆኖ አንድ ትንቢት ምዕመናንን የሚያሳፍር ፣ ቅስማቸውን የሚሰብርና ፣ የሚያስፈራራ ብቻ ሆኖ ቢቀርብ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ዓይነቱ ትንቢት ከርኩሳን መናፍስት የሚመነጭ ነው ፣ አለዚያም ነቢዩ የሚጠላቸውን ሰዎች ለማዋረድ ሆን ብሎ ከራሱ ሃሳብ የሚናገረው ነው። ያለገደብ ሰውን የሚክብና የሚያሞካሽ ትንቢትም ከመንፈስ ቅዱስ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሰውን ሳይሆን ኢየሱስን ነው የሚያከብረው (ዮሐ16 : 14)። ይህ ዓይነቱ ትንቢት ከሰዎች የሆነ ጥቅም ለማግኘት ተፈልጎ ከሥጋ የሚነገር ትንቢት ነው። አንዳንድ ጊዜ ነቢዩን ራሱን የሚያሞግስና ከአድማጮቹ አክብሮትን የሚጠይቅ ትንቢትም ይነገራል! መዚህ መልክ የሚቀርብ ትንቢት ጨርሶ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።

## ➢ በግል በሚገኝ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ትንቢት ይገመገማል
(ሉቃስ 24 : 32 ፣ 1ኛ ዮሐ 2 : 20 ፣ 26 - 27)

በተጠቀሱት የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች መሠረት አንድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን የተሳሳተን መልዕክት በመንፈስ መለየት ይችላል። ለዚህ ይበቃ ዘንድ ግን እለት በዕለት በልብና በሕሊና ንፅህና መመላለስ ይኖርበታል። ትንቢት በዚህ መንገድ ሲመረመር ግለሰቡ ትክክለኛ ያልሆነውን መልዕክት ለራሱ ከመውሰድ እንዲቆጠብ ያደርገዋል እንጂ ተነስቶ ተናጋሪውን ሰው ለማረም አያስችለውም። በውስጡ ከተሰማው በስተቀር ሌላ የሚያሳምንበት ማስረጃ የለውምና።

### ➢ ውጤቱን በመከታተል ትንቢት ይመዘናል
(ዘዳ 18 ፡ 21 - 22 ፣ ኢሳ 55 ፡ 10 - 11)

በእግዚአብሔር ስም የተነገረ ትንቢት ልክ እንደተነገረው ሁኔታ እንዲፈጸም ይጠበቃል። ይህ መመዘኛ የሚሠራው ወደፊት ስለሚፈጸም ነገር ለተነገሩ የትንቢት መልዕክቶች ነው። ትንቢቱ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንደሚፈጸም የተነገረ ከሆነ የተቀጠረለትን ጊዜ ጠብቆ መፈጸም ይኖርበታል። አብዛኛውን ጊዜ ግን ትንቢቶች ቅደመ-ሁኔታዎችን የሚያካትቱ ናቸው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ትንቢቶች የተጠቀሰው ቅድመ-ሁኔታ ካልተሟላ በስተቀር አይፈጸሙም። እንግዲህ የትንቢቱን ተፈጻሚነት ለመከታተልም ሆነ ፣ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈለጉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ለማሟላት ትንቢት ሲነገር ተጀምሮ እስኪጨረስ በፍጹም ጸጥታ በማስተዋል ማድመጥ ይገባል። ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን እንዲሰፍን መሪዎች ተግተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በጥንቃቄ የተደመጠ ትንቢት ክትትል ተደርጎበት ያለመፈጸሙ ከተረጋገጠ ፣ መሪዎች ነቢዩን ሊመክሩት ያስፈልጋል። ጉዳዩን ለጉባኤው ማስረዳት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

### ➢ ከተናጋሪው የክርስትና ሕይወት አቋም ትንቢት ይመዘናል
(ኤር 23 ፡ 11 - 18 ፣ ሕዝ 13 ፡ 19 ፣ ሚኪ 3 ፡ 5 ፣ ማቴ 7 ፡ 16)

የቀደሙት የእስራኤል ነቢያት አገልግሎታቸው የተበላሸው ሕይወታቸው ከመበላሸቱ የተነሳ ነበር። ዛሬም ችግሩ ያው ነው። የገንዘብ ፍቅር በጉልህ የሚታይበት ነቢይ ጥቅም እንዲያስገኝለት ፈልጎ ከራሱ ሃሳብ ትንቢት ሊናገር ይችላል። በስውር ዝሙትን የሚለማመድ ነቢይ ፍላጎቱን ለማሟላት የሚረዳውን ትንቢት ሊናገር ይችላል። በቤተክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል ቢፈጠርና የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው ራሱን የአንድ ቡድን ደጋፊ ቢያደርግ ሌላውን ቡድን የሚቃወም ትንቢት ለመናገር ራሱን ሊያሰልፍ ይችላል። ይህን ዓይነት ስህተቶች የሚፈጠሩት በአንዳንዱ ሁኔታ ሆነ ተብሎ ታቅዶ በአእምሮ የሚፈጸም ሲሆን ፣ በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ በስሜት ከመወሰድ የተነሳ የክፉ መንፈስን ወይም ከራስ ስሜት የሚመነጭ ድምፅን የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ እንደሆነ አድርጎ ከመውሰድ የተነሳ ነው።

**ይህን ክፍል ስደመድም ሁለት ነጥቦችን አበክሬ አሳስባለሁ፦**

☞ የትንቢት ስጦታ ጤናማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ሆኖ ለምእመናን የበረከት ምክኒያት እንዲሆን ፣ ሁሉ በአግባብና በሥርዓት እንዲፈጸም ፣ የብዙዎችን የተጋ ተሳትፎ እንደሚጠይቅ ተመልክተናል። ጥንቃቄ በማይደረግበት ሁኔታ ይህን ጸጋ ሥራ ላይ ማዋል ከፍተኛ ችግርን መጋበዝ ነው። በዚህ ዓይነት ውድቀትን የሚጋብዝ በዘመናችን ያለ አዝማሚያ ፣ የትንቢት ስጦታ አላቸው የሚባሉ ግለሰቦችን በየመንደሩ እየፈለጉ ለግል ትንቢት እንዲነገር



የሚደረገው አካሄድ ነው። ይህ ዓይነቱ አድራጎት አዲስ ኪዳናዊ አይደለም ፣ የብዙ ሰዎችን ሕይወትም አበላሽቷል። ትንቢት ፈላጊዎችም ሆናችሁ ትንቢት ተናጋሪዎች ከዚህ ዓይነት አሠራር ውስጥ ራሳችሁን እንድታተርፉ አሳስባለሁ።

☞ ሌላው ማሳሰቢያ የተደጋገመ ነው። እግዚአብሔር የመሪነት ጸጋን የሰጠበት አንዱ ምክኒያት ሁሉ በአግባብና በሥርዓት እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን እንድትተዳደርበት ነው። ሥርዓትን እንዲያስጠብቁ እግዚአብሔር የሰማይ መላዕክትን በቤተ ክርስቲያን አያሰማራም። መሪዎች በእግዚአብሔር ጸጋ ተደግፈውና በቃሉ ታጥቀው ቤተ ክርስቲያንን ከዚህ አደጋ እንዲታደጉ በጌታ ፍቅር እለምናለሁ።

---

## ማስታወሻዎች


1. 1ኛ ቆሮ 13 ፡ 1 - 3
2. 1ኛ ቆሮ 13 ፡ 4 - 7
3. Fee. GD and Stewart. D 1993. How to read the Bible for all its worth. 2nd Ed. P 26 ፣ 64
4. 1ኛ ቆሮ 14 ፡ 27 - 28
5. Ramm. B 1970. Protestant Biblical Interpretation. 3rd Ed. PP 107.
6. Ibid. PP 104
7. Central Statistics Authoritty. 1999. The 1994 population and housing census of Ethiopia. Vol II. P 56
8. 1ኛ ቆሮ 14 ፡ 3
9. 1ኛ ቆሮ 14 ፡ 24 - 25
10. 1ኛ ቆሮ 14 ፡ 19 ፣ 1ኛ ተሰ 5 ፡ 20 - 21 ፣ 1ኛ ዮሐ 4 ፡ 1
11. ኤር 23 ፡ 18 ፣ 21 - 22

# III. የዕውቀትን ቃል መናገርና የፈውስ ስጦታዎች

## መግቢያ

እነዚህ ሁለት የጸጋ ስጦታዎች በአንድ ርዕስ ስር የተጠቃለሉበት ምክኒያት ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቤተክርስቲያን መድረኮች እየተለመደ የመጣን የተዛባ አሠራር ለማሳየት ስለፈለግሁ ነው። በርካታ አገልጋዮች ለሕመምተኞች በነፍስ ወከፍ መጸለይን ትተዋል። ከዚያ ይልቅ ከመድረክ የተለያዩ የበሽታ ስሞችን በመጥራት ፣ ሰዎች ከበሽታዎቹ መፈወሳቸውን ያውጃሉ። የሚታወጀው ፈውስ ብዙ ነው፣ "ተፈውሻለሁ" ብለው የሚመሰክሩ ሰዎች ግን አበዛኛውን ጊዜ አያጋጥሙንም።

አሠራሩን ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ ስንመዝነው የተዛባ ነው። የበሽታዎች ዝርዝር ተነግሮ ፈውስ የሚታወጅበት ሁኔታ የዕውቀትን ቃል የመናገር ስጦታን ይመስላል። ይህን ስጦታ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሞክሮዎችን ስናስታውስ ፣ ከፈውስ ጋር በተያያዘ ተግባራዊ የሆነበት ጥቂት ጊዜያት ቢኖሩም በሌሎች የተለያዩ ሁኔታዎች ጥቅም ላይ ውሏል። በኛ መካከል ግን ይህ ስጦታ ከፈውስ ጋር ብቻ የተቆራኘ ይመስላል። ስለዚህም የስጦታውን እውነተኛነት እንድንጠይቅ ያስገድደናል። ሌላው የተዛነፈው ሁኔታ የፈውስ አገልግሎት በዚህ መልኩ ብቻ እንዲቀርብ መደረጉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እጅ ጭኖ መጸለይን በዋነኛነት አስቀምጦ ሌሎች የተለያዩ መንገዶችንም ያሳያል። ብዙ ፈውስ በድፍረት እየታወጀ ተፈጻሚ አለመሆኑም ከአዲስ ኪዳን ትምህርትና ተሞክሮ ጋር አብሮ አይሄድም። በጌታችን በኢየሱስና በሐዋርያት አገልገሎት ለፈውስ የተጸለየላቸው አብዛኛዎቹ ሰዎች ይፈወሱ ነበርና።

በአዲስ ኪዳን እንደምናነበው አስደናቂ ፈውሶች ሲፈጸሙ ሕዝብ ተደስቶ ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጥ ነበር። ዛሬ በእኛ አብያተክርስቲያናት በትልቅ አዋጅ የሚደረግ የፈውስ አገልግሎት ግን በአብዛኛው የክርክር ፣ የቅሬታና የእሮሮ ምክኒያት ሆኗል። ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች በጉዳዩ ተቸግረዋል። ርዕሱን በተመለከተ ጠቃሚ የሆነ ጽሑፍም በቅርቡ አንብቤአለሁ[1]። ይህን አጥፊ አዝማሚያ ፊት ለፊት ልንጋጠመውና ልናስተካክለው ጊዜው እየረፈደብን ነው። በዚህ ርዕስ የማቀርበው ሃሳብ ወሳኝ እርምጃ ለመውሰድ ጠቃሚ አስተዋፅዖ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ።



### ሀ) የችግሩ አስከፊ ገጽታዎች

የዕውቀትን ቃል ከመናገር ጋር የተያያዘ የፈውስ አዋጅን ችግሮች ስዘረዝር ጤናማ በሆነ መልኩ እነዚህ ስጦታዎች የሚገለጡበት ጊዜ የለም ለማለት አይደለም። ሕይወታቸውን በጥንቃቄ እየገዙ በነዚህ ስጦታዎች እግዚአብሔር የሚገለገልባቸው ሰዎች አሉ። በአብዛኛው የምናየው ግን እውነተኛ አገልግሎት ሳይሆን ፣ ከሰዎች ሞገስን ወይም ጥቅምን በመፈለግ የሚደረግ የማስመሰል እንቅስቃሴ ነው። ይህ ዓይነቱ "አገልገሎት" ነው በአስከፊ ገጽታዎቹ እያሳሰበን ያለው።

የሚነገሩት የፈውስ አዋጆች አሻሚ ናቸው። ሰው ተለይቶ ስለማይነገር ጉዳዩን ተከታትሎ አገልጋዩን መጠየቅ አይቻልም ፣ የተጠቀሱት በሽታዎች ያሉባቸው ሰዎች በሙሉ ተፈውሳችኋል ስለሚባሉ ግለሰቦቹ ተፈውሻለሁ እያሉ በየጎረቤቱና በየመሥሪያ ቤቱ መመስከር ይጀምራሉ። የኤድስ በሽታም በአዋጅ ውስጥ የሚካተትበት ጊዜ አለ። ይህ በሽታ ያለባቸው ሰዎችም ራሳቸውን ለሕብረተሰቡ ያጋልጣሉ። አዋጁ ግን የእግዚአብሔር ሳይሆን የሰው ስለሆነ ፈውስ አይኖርም። በተለይ ሕመሙ ለሞት የሚዳርግ ዓይነት ከሆነ መላው ሕብረተሰብ እስከፍጻሜው ይከታተለዋል ፣ ሕመምተኛውና ሌሎች ክርስቲያኖች እየተሸማቀቁ ፣ የማያምኑት ደግሞ እያሾፉ። ምሥጢሩ ያልገባቸው ክርስቲያኖች ፣ ከሕመምተኛው ጭምር በእግዚአብሔር ላይ እንኳን ጥርጥር ያድርባቸዋል። የማያምኑ ሰዎች ደግሞ ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናትን በጅምላ "የውሸታሞች ጎሬ" ብለውታል። እንግዲህ ተከታትለው ካረጋገጡት ሁኔታ ውሸታም መሆናችንን የተረዱ ሰዎች ወንጌልን ከእኛ እንዴት ሊቀበሉ ይችላሉ? ከአዳራሽ ውጪ በተተከለ ሜጋፎን አካባቢውን ብናናውጠው እንኳን የሚመጣ ለውጥ የለም።

"ብዙዎች ተፈውሳችኋል ተብለው ለምን አልተፈወሱም?" ተብሎ ሲጠየቅ ፣ ሕመምተኞቹ እምነት ስለሌላቸው ነው ብለው አገልጋዮች ይመልሳሉ። ይህ ምላሽ ግን ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። በአዲስ ኪዳን ዘመን ፈውስ ፈልገው የሚመጡ ሰዎችንና በአሁኑ ዘመን ፈውስ ፈልገው የሚመጡ ሰዎችን ምን ይለያቸዋል? እነዚያ በመጡ ዕለት ወንጌል ሰምተው ሲጸለይላቸው ሁላቸው ይፈወሱ ነበር። የእምነታቸው መግለጫ ፈውስ ለማግኘት መፈለጋቸውና ኢየሱስ ሊፈውሳቸው እንደሚችል ማመናቸው ብቻ ነበር[2]። የእምነት ጥያቄ ሳይነሳ ጌታ በርኅራኄ የሚፈውሳቸውም ብዙዎች ነበሩ። ስለእምነት ልዩ ሴሚናር አይሰጣቸውም ነበር። የዛሬዎቹ ሕመምተኞች እንዲያውም ስለእምነት የተሻለ ግንዛቤ አላቸው። በተደጋጋሚ ቤተክርስቲያን ስለሚመጡ ስለእምነት ይሰማሉ። እንዲያውም ፈውስ ከሚፈልጉ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ናቸው። ልዩነት ያመጣው የሕመምተኞቹ እምነት አይደለም። ልዩነት ያመጣው የአገልጋዮቹ ማንነት ነው። ኢየሱስ ፣ ሐዋርያቱና ወንጌላዊያኑ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው የፈውስ ጸጋ በላያቸው ላይ ነበር ፣ የዛሬዎቹ አገልጋዮች ግን እውነተኛ ጸጋ የሌላቸው ደፋር አስመሳዮች ናቸው።

ብዙዎች የታዘቡት ሌላው ሁኔታ በብዛት የሚታወጁት ፈውሶች ጉልህ የሆኑ የአካል ጉዳቶች ሳይሆኑ ፣ ጭንቀት ፣ ራስ ምታት ፣ ፍርሃት ፣ የሆድ ሕመምን የመሳሰሉ ውስጣዊ የሕመም ስሜቶች ናቸው። ይህን የመሳሰሉ የሕመም ስሜቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማንም የሚያጋጥሙ ናቸው። ስሜቶቹ ይመጣሉ ይሄዳሉ። የሕመሙ ስሜት ሲወገድ ፣ ከታወጀው ፈውስ የተነሳ ይሁን ወይስ ከስሜቱ ተለዋዋጭ ባሕርይ የተነሳ ፣ ለመለየት ያዳግታል። በማያምኑት ዘንድም የማሾፊያ ምክኒያት ሊሆን ይችላል። በአንጻሩ ግን በአዲስ ኪዳን የተዘገቡ ፈውሶች ሕብረተሰቡ ሁሉ የሚያውቃቸው ከፍተኛ ሕመሞች ነበሩ። ለምጽ ፣ ዐይነ ስውርነት ፣ ድንቁርና ፣ ሽባነት ፣ ጎባጣነት ወዘተርፈ። ሕመሙ እንደታወቀው ሁሉ ፈውስ ሲፈጸምም በገሃድ ስለሚታይ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ ነበር ፣ ሰዎችም ወደ ጌታ ይመለሱ ነበር።

ከቤተሰብ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የመናፍስት አሠራር የሕመም ምክኒያት መሆኑ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እየገነነ የመጣ ሌላው የአዋጅ ርዕስ ነው። ይኸኛው ርዕስ በተናጋሪዎቹ ዘንድ በጥንቃቄ የታሰበበት ይመስለኛል። ምክኒያቱም በሰሚዎች ዘንድ በቀላሉ ሊታመን ይችላል ፣ ለብዙዎች ከወላጆቻቸው ጀምሮ በቀደሙት ትውልዶች ሁሉ የመናፍስት አምልኮ የተንሰራፋ ነውና። ጉዳዩ ግን ከመድረክ የሚነገርለትን ያህል በጥንቃቄ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ሕይወት እውነት ሊሆን ይችላል ወይ? ቃሉ የሚያስተምረን በክርስቶስ የሚያምን ከሰይጣን መንግሥት ነፃ ወጥቶ ወደ ክርስቶስ መንግሥት እንደተሻገረ ነው።

> *"አንተም ዓይናቸውን ትከፍታለህ ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ፣ ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ትመልሳቸዋለህ..." (ሐዋ 26 : 18) "እርሱ ከጨለማ ግዛት ታደገን ፣ ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን" (ቆለ 1 : 13)::*

ሽግግሩም የሚከናወነው ከክርስቶስ ጋር መሞታችንን ስናምን ነው[3]። የክርስቶስ ሞት ሞታችን ይሆንና ከሰይጣን መዝገብ ተሰርዘን በመንግሥተ-ሰማያት መዝገብ እንጻፋለን። አንድ የምዕራብ ሸዋ ክርስቲያን በቅርቡ የመሰከረልኝ ይህን እውነት ያጸናል። የዚህ ወንድም እናት በከፍተኛ ደረጃ ሰይጣንን የሚያመልኩ ናቸው። ከብዙ ልጆቻቸው መካከል ታሪኩን የነገረኝ ሰውና አንድ ታናሽ ወንድሙ ጌታን ተቀብለዋል። እናትየው ወደ ጠንቋይ ቤት ሄደው ስለ ልጆቻቸው ሲለምኑ ጠንቋዩ "ከሁለት ልጆችሽ ስም በስተቀር የሌሎቹ ልጆችሽ ስም ሁሉ በመዝገቤ አለ" ብሎ ተናገራቸው።

እንግዲህ ክርስቲያን ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ይመን ፣ ወይስ ከመድረክ የሚታወጀውን አዋጅ ይመን? የክፉዎች መናፍስት ጣልቃገብነት የሚነገርለትን ያህል ከሆነማ በወንጌል የታወጀልንን ነፃነት ጥያቄ ውስጥ የሚከትተው ይሆናል። አዘወትረው ይህን የሚመስል አዋጅ የሚያውጁትስ ሳያውቁት የሰይጣንን ሥልጣን በየዋሆች መካከል የሚያሰርጹ



አይሆኑም ወይ? ይህን ዓይነት መልዕክት በተደጋጋሚ ሲሰሙ የዋህ የሆኑ ሰዎች ነገሩን ተቀብለውት በሚሰማቸው የህመም ስሜት ላይ የሰይጣን ጥቃት ሰለባ ለመሆን ይዳረጋሉ። "እንደ እምነትህ ይሁንልህ" የሚለው ቃል ለአሉታዊ ክስተቶችም ተግባራዊ ይሆናልና።

ሌላው እጅግ አሳዛኝ ሁኔታ "ተፈውሳችኋል" ለሚባሉት ሰዎች ከመድረክ የሚሰጣቸው ምክር አለመኖሩ ነው። አገልጋዮቹ ኃላፊነት ስለማይሰማቸው ፣ ወይም ለራሳቸውም ግንዛቤ ስለማይኖራቸው ይሆናል ምክር የማይሰጡት። አዋጁን የተቀበሉ ሕመምተኞች መፈወሳቸውን ሳያረጋግጡ ለሕብረተሰቡ የሚሰጡት ምስክርነትና ያለአግባብ ራስን ማጋለጥ የዚህ ግድፈት አንዱ ውጤት ነው። ሌላው አስከፊ ውጤት በየእለቱ መድኃኒት እየወሰዱ በሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ሳይፈወሱ መድኃኒት ማቋረጣቸው ነው። ከፍተኛ የልብ ድካም ፣ የደም ግፊት ፣ የስኳር ሕመም ፣ የሚጥል በሽታ በዚህ ደረጃ የሚቆጠሩ የተለመዱ በሽታዎች ናቸው። ሕመምተኛው መድኃኒቱን እንዳቋረጠ ሕመሙ በአፋጣኝ ይብስበታል ፣ በአፋጣኝ ወደ መድኃኒቱ ካልተመለሰም ለሕይወት ሕልፈት ሊዳረግ ይችላል። በዚህ ዓይነት ወደአሳዛኝ ፍጻሜ የመጡም አሉ። ይህ ዓይነቱ አሳዛኝና አሳፋሪ ድርጊት ለእግዚአብሔር ስምና ለቤተክርስቲያን ሕልውና ምን ያህል ነቀፌታ እንደሚያመጣ መገመት አያዳግትም። በቶሎ ይህ ቀውስ ካልተስተካከለ ወደፊት የበለጠ የሚያስከፋ መዘዝ ሊያመጣ እንደሚችል እስባለሁ፦ በሕግም ሊያስጠይቅ ይችላል!

ለበረከት በታሰበ አገልግሎት ይህ ሁሉ ትርምስና ጉዳት በጭራሽ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። በእግዚአብሔር እርዳታ በፍጥነት ካልገታነው በስተቀር የሰዎች እምነት ተሟጦ ስለፈውስ ማንሳት የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህን ምዕራፍ ከመደምደሜ በፊት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ጥቂት ሃሳብ እሰጣለሁ።

## ለ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የዕውቀትን ቃል መናገር ስጦታ

የዕውቀትን ቃል መናገር ስጦታ እንደስጦታ በስም ተጠቅሶ የምናገኘው በ1ኛ ቆሮ 12 : 8 ላይ ብቻ ነው። ከትምህርት አኳያ ስለስጦታው ምንነት ግዛቤ የምናገኘው ስጦታው የተገለጠበትን ቃላት በማጤን ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስጦታው ተግባራዊ ከሆነባቸው ከብዙ ምሳሌዎች ግንዛቤ እናገኛለን። አዲሱ መደበኛ ትርጉም "የዕውቀትን ቃል መናገር" ሲለው የ1954 የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ትርጉም "ዕውቀትን መናገር" ይለዋል። "የዕውቀት ስጦታ" አልተባለም ፣ እንደዚ ቢባል ኖሮ እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ማወቅን ያመለክታል። ስጦታው የዕውቀትን ቃል መናገር ሲባል ፣ ለተወሰነ ዓላማ እግዚአብሔር ዕውቀትን ሲገልጥ ያንን ዕውቀት ማስተላለፍን ያመለክታል። የዕውቀት "ቃል" መባሉ የሚገለጠው ዕውቀት ውስን መሆኑንም ያመለክታል። በዚህ መልኩ ሰፊ ሃሳብ ይዞ ከሚገለጠው ከትንቢት ስጦታ ይለያል። ስጦታው ከተገለጠበት ቃል ትንታኔና በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናያቸው ብዙ ምሳሌዎች

በመነሳት ፣ የዕውቀትን ቃል መናገር ስጦታን እንደሚከተለው ልንተረጉመው እንችላለን፦

> *"የዕውቀትን ቃል መናገር ስጦታ ቅጽበታዊና ተአምራዊ በሆነ መንገድ ለተወሰነ ዓላማ መንፈስ ቅዱስ ለሰው መረዳትን የሚሰጥበትና መረዳቱን የተቀበለው ሰው ተፈላጊውን እርምጃ የሚወስድበት ስጦታ ነው።"*

እንደ ሌሎቹ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ዕውቀቱ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ሲፈልግ እንጂ ባለስጦታው በሚፈልግበት ጊዜ አይደለም። ስጦታው ተግባራዊ የሆነባቸውን ምሳሌዎች ስንመለከት ስለስጦታው ባሕርያት የበለጠ ግንዛቤ እናገኛለን።

## ➢ የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች

- የሳኦል አህዮች መገኘታቸውን ሳሙኤል ያወቀበት (1ኛ ሳሙ 9 ፡ 20)
- ሳሙኤል ዳዊትን ለይቶ የቀባበት መረዳት (1ኛ ሳሙ 16 ፡ 6 - 13)
- ኤልሳዕ የሦርያ ንጉሥን ምሥጢር ያወቀበት መንገድ (2ኛ ነገ 6 ፡ 8 - 12)
- ኤልሳዕ የግያዝን ማጭበርበር ያወቀበት መንገድ (2ኛ ነገ 5 ፡ 20 - 27)
- ነህምያ ካህኑ ሸማያ ያሰበውን ተንኮል ያወቀበት (ነህ 6 ፡ 10 - 12)

## ➢ የአዲስ ኪዳን ምሳሌዎች

ብዙዎቹ የአዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ከኢየሱስ ሕይወት የተወሰዱ ናቸው። ምናልባት አንዳንዶች ፣ ኢየሱስ አምላክ ስለሆነና ሁሉን ነገር ስለሚያውቅ የዕውቀትን ቃል መናገር ስጦታ እርሱን አይመለከተውም ብለው ያስቡ ይሆናል። ይህ አስተሳሰብ ግን ትክክለኛ አይደለም። የፊሊጵስዩስ መጽሐፍ ትክክለኛውን ሁኔታ ይገልጽልናል።

> *"እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም ፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰው አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ ፣ ሰው ሆኖ ተገልጦም ራሱን ዝቅ አደረገ" (ፊሊጵ 2 ፡ 6 - 8)።*

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መስዋዕት እንዲሆን ኢየሱስ ፍጹም ሰው ሆኖ በምድር መመላለስ ነበረበት። ለዚህ ነው ራሱን ከመለኮታዊ ችሎታዎች በፈቃደኝነት ባዶ ያደረገው። በምድር በተመላለሰበት ዘመን በኢየሱስ



ሕይወት የታዩት ተዓምራዊ ድርጊቶች ሁሉ በሙላት በውስጡ ከሚሠሩት የጸጋ ስጦታዎች የተነሳ ነበረ[4]። ከዚህም የተነሳ ነው ኢየሱስ ለሕይወታችን ምሳሌ ሊሆን የሚችለው። የምድር ተልዕኮውንም ሊጨርስ ሲል በጸለየው ጸሎት "እንግዲህ አባት ሆይ ፣ ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክብረኝ" (ዮሐ 17 ፡ 5) ማለቱ በፈቃዱ ወደ ተወው መለኮታዊ ችሎታ መመለሱን ያመለክታል። ከዚህ ማብራሪያ በኋላ ወደ ምሳሌዎቹ እንመለሳለን፦

- ኢየሱስ ናትናኤልን ከበለስ በታች ሆኖ ያየበት (ዮሐ 1 ፡ 49)
- ኢየሱስ የሳምራዊቷን ሴት ምሥጢር ያወቀበት (ዮሐ 4 ፡ 17 - 18)
- ኢየሱስ የባለሥልጣኑን ልጅ የፈወሰበት (ዮሐ 4 ፡ 49 - 50)
- ገንዘብ በሆዱ ውስጥ ያለበትን ዓሣ ለይቶ ያወቀበት (ማቴ 17 ፡ 27)
- ደቀመዛሙርት ስለሹመት የተከራከሩበትን ፣ የፈሪሳዊያንን ስውር ሃሳብ ፣ አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ፣ ወዘተርፈ ያወቀበት
- የሐናኒያና ሰጲራን ግብዝነት ጴጥሮስ ያወቀበት (ሐሥ 5 ፡ 3)
- ፊሊጶስ ስለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መረጃ ያገኘበት (ሐሥ 8 ፡ 26 - 29)
- ኤንያ የተፈወሰበት (ሐሥ 9 ፡ 34)
- ጴጥሮስ የቆርኔሌዎስን መልዕክተኞች ያወቀበት (ሐሥ 10 ፡ 19 - 20)
- የልስትራው ሽባ ሰው ለመፈወስ እምነት እንዳለው ጳውሎስ ያወቀበት (ሐሥ 14 ፡ 9 - 10)

## ➢ ከምሳሌዎቹ የምንማረው

ምሳሌዎቹ በዋናነት የሚያሳዩን የተገለጡት መረጃዎች አሻሚ አለመሆናቸውን ነው። የሳኦል አህዮች መገኘታቸውን ሳሙኤል ሲያውቅ በግልጽና በድፍረት ነው የተናገረው፦ ሳኦል ገና ስለአህዮች ሳይናገር "ከሦስት ቀን በፊት የጠፉት አህዮች ተገኝተዋል" ነው ያለው። ኤልሳዕ የግያዝን ማታለል ሲገልጸው ማስተባበል በማይቻልበት መንገድ ነበር። ኢየሱስ ናትናኤል ተቀምጦ የነበረበትን ቦታ በትክክል ሲነግረው ናትናኤል ወዲያውኑ አመነበት። የሳምራዊቷ ሴትም ምሥጢር በትክክል ሲገለጥ በኢየሱስ አመነች ፣ ለከተማዋ ሰዎችም ምስክር ለመሆን ቻለች። የሐናንያና ሰጲራን ውሸት ጴጥሮስ በትክክል ስላወቀ ነው በድፍረት የፍርድ ቃል የተናገረው ፣ እግዚአብሔርም ቃሉን አጸናለት። ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ሳይረዳ እንደዚሁ በድፍረት ሽባውን ሰው

"ተነሳና ቁም!" ብሎ በአደባባይ የጮኸ ቢሆን ምን ይፈጠር ነበር? የእግዚአብሔር ሰው አለመሆኑ እጅ በእጅ ስለሚታወቅ የሰበከውም ወንጌል ተቀባይነት አያገኝም ነበር። የዕውቀትን ቃል ስጦታ በመጠቀም በግልጽ ስለተናገረ ፣ የተፈጸመው ፈውስ ለእግዚአብሔር ክብር ሆነ ፣ የተሰበከውም ወንጌል በምልክት ጸና።

ስለፈውስም የተነገሩት የዕውቀት ቃላት የተወሰነን ሕመምተኛ የሚመለከቱና በእርግጠኝነት የተነገሩ ናቸው። በእያንዳንዱም ሰው ላይ የተነገረው ቃል ተፈጽሟል። ዛሬ ከየመድረኩ የሚነገረው የፈውስ አዋጅ በአብዛኛው አሻሚ ነው። የሚገለጠው ፈውስ ከተወሰነ ግለሰብ ጋር አይያያዝም። ስለዚህም ሕመምተኞች ለማመንታት ይዳረጋሉ። ስለእኔ ነው የተናገረው ብለው ራሳቸውን ያሳመኑም ምንም ውጤት ሳያገኙ ሲቀሩ ግራ ይጋባሉ። አገልጋዩም ከግለሰብ ጋር የተያያዘ ቃል ባለመስጠቱ እጅ ከፍንጅ ስለማይያዝ በሌሎች መድረኮች ተመሳሳይ ድርጊቶች እየፈጸመ ይቀጥላል። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌነት የሌለው በዘይ የተፈጠረ ነው። መገታት ይኖርበታል።

## ሐ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የፈውስ አገልግሎት

በዚህ ርዕስ ፈውስን የሚመለከቱ ሃሳቦችን በሙሉ አንመለከትም። ከፈወስ አገልግሎት አፈጻጸም ላይ በምንቸገርባቸው ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን።

### ➢ የፈውስ አገልግሎት ለሁሉ ክርሰቲያኖች ነው ወይስ የተለየ ስጦታ ለተሰጣቸው?

መፈወስ በስጦታ መልክ በ1ኛ ቆሮ 12 ፡ 9 ላይ መጠቀሱ ለሁሉ ክርስቲያኖች እንዳልሆነ ያመለክታል። ክርስቲያኖች ሁሉ ግራና ቀኝ የፈውስ አገልግሎት መስጠት ቢችሉ ኖሮ የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሆኖ ሊጠቀስ አያስፈልገውም ነበር። የፈውስ አገልግሎት ለሁሉም ክርስቲያኖች ነው የሚለው ሃሳብ መሠረት የሚያደርገው ማር 16 ፡ 18ን ነው። ስለዚህ የዚህን ጥቅስ ዐውድ ትኩረት ሰጥተን መመልከት ያስፈልገናል። ሃሳቡ የጀመረው ቁጥር 17 ላይ ነው። "የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል..." በማለት። የሃሳቡ ቁልፍ ያለው "ምልክት" በሚለው ቃል ላይ ነው። የተዘረዘሩትን የሚመስሉ ተዓምራዊ ክስተቶች በሕይወቱ ሲያጋጥሙት በጌታ ውስጥ መሆኑን ያረጋግጥለታል። ሁኔታው ጌዲዎን በምድያም ላይ እንዲዘምት የተሰጠውን ምልክትና ሕዝቅያስ መፈወሱን እንዲያምን የተሰጠውን ምልክት ይመስላል[5]። የየግላችንን ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ብናስታውስ ጌታን በተቀበልንበት የመጀመሪያዎቹ ቀናትና ወራት በርከት ያሉ ተዓምራት አጋጥመውናል። እያንዳንዱ ተዓምርም የጌታን ሕልውና ስላሳየን በእምነታችን እንድንጸና እጅግ ረድቶናል። በግል ሕይወቴ የመጀመሪያውን ጉልህ የፈውስ ተዓምር ያየሁት ጌታን በተቀበልሁ በ3ኛው ቀን ለታናሽ ወንድሜ በጸለይሁለት ጸሎት ነበር።



ክርስቲያን በጌታ ሲቆይና ሕይወቱ ሲጸና ፣ ልዩ ስጦታ የተቀበለ ካልሆነ በስተቀር የፈውስ ክስተቶች እየቀነሱ ሊሄዱ ይችላሉ። በእምነቱ የተደላደለ ስለሆነ ምልክቶችን አዘወትሮ ማየቱ አያስፈልገውምና። ይህም ሲባል በበሳል ክርስቲያን ጸሎት ፈውስ ጨርሶ አይፈጸምም ለማለት አይደለም። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ ፣ በመደበኛ መልኩ በፈውስ የሚያገለግል ሰው በሌለበት ሁኔታ ፣ በተለይም ለሕይወት አስጊ የሆነ ሕመም በሚያጋጥምበት ጊዜ የምዕመናንን ጸሎት እግዚአብሔር ይመልሳል። ሁኔታውን ከምዕመናን ምስክርነትና የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ጋር ማመሳሰል ይቻላል። አማኝ ሁሉ ለክርስቶስ እንዲመሰክር ይጠበቅበታል[6]። ይህ እንደተጠበቀ ሳለ ወንጌል ሰባኪነት ደግሞ ራሱን የቻለ የጸጋ ስጦታ ሆኖ ተመዝግቧል[7]። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ልዩነቱ የሚገኘው ፍሬ መጠን ነው፦ ምዕመን ወጥቶ ለ100 ሰዎች ቢመሰክር ጌታን የሚቀበሉ 2 ወይም 3 ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ የተሰጠው ሰው ወጥቶ ለ100 ሰዎች ቢመሰክር 20 እና 30 ሰዎች ጌታን ሊቀበሉ ይችላሉ። ክርስቲያን የመፈወስ ስጦታ የተሰጠውና ያልተሰጠው መሆኑን የሚፈትነውም በሚገኘው ፍሬ ብዛት ነው።

የፈውስ በመደበኛነት አገልግሎት ለሁሉ ክርስቲያን አለመሆኑን በዚህ መልኩ ከተገነዘብን በኋላ መደበኛ የፈውስ አገልጋዮች የትኞቹ እንደሆኑ ባጭሩ እንመለከታለን። አዲስ ኪዳን የሚያሳየን መደበኛ የፈውስ አገልጋዮች ሁለት ዓ ይነት እንደሆኑ ነው። አንደኛው ወገን ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ፈውስን እንደ ጸጋ ስጦታ የተቀበሉ ሰዎች ናቸው። በተግባር ሲገለጥ ይህ ስጦታ ሙሉ በሙሉ የታየው በሐዋርያትና በወንጌል ሰባኪዎች አገልግሎት ነበረ። ከወንጌል ሰባኪዎች እስጢፋኖስንና ፊሊጶስን መጥቀስ እንችላለን። ሁለተኛው ወገን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ናቸው[8]። የተጠቀሰውን ቃል ስናጤነው ፈውሱ የሚከናወነው የሽምግልና ሹመት ስላለ ብቻ አይደለም። "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ ኃይል ታደርጋለች" እንደሚለው ፣ በጥንቃቄ በሚመራ ሕይወት በጽድቅ መመላለስም ያስፈልጋል።

### ➢ ሕክምናና መለኮታዊ ፈውስ

ሕክምናና መለኮታዊ ፈውስ አብረው አይሄዱም ብለው የሚያምኑ ወገኞች አሉ። እንደዚህም የሚያስተምሩ ወገኖች አሉ። ከጌታ ፈውስን ለመቀበል ተስፋ የሚያደርግ ሰው የሚወስደውን መድኃኒት እንዲያስወግድም ይጠየቃል። ማንኛውም ዓይነት ሕመም ያጋጠመው ክርስቲያን መለኮታዊ ፈውስ እንዲጠብቅ እንጂ ወደ ሕክምና እንዳይሄድ ይመከራል ፣ ወደ ሕክምና የሚሄድም እግዚአብሔርን እንደበደለ ይቆጠራል። ይህ ዓይነቱ አመለካከት የሰፈነው በአገራችን ከተከሰተው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ወዲህ ነው። ደግነቱ ዓመታቱ እየተራዘሙ ሲሄዱ የዘረዘርኳቸው አመለካከቶች እየደከሙ መጥተዋል ፣ ሆኖም ለፈውስ የተጸለየለት ሰው የሚወስደውን መድኃኒት ወዲያውኑ ያቋርጥ የሚለው አስተሳሰብ የቀጠለ ሆኖ ችግር እየፈጠረ ነው።

የሕክምና እርዳታ ተቀባይነት እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቁማል። የሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎት ባልደረባ ፣ ከብዙ የአገልግሎት ዘመን በኋላ ባለመድኃኒቱ ሉቃስ ተብሎ ተጠርቷል (ቆላ 4 : 14)። ታላላቅ ፈውሶች በሐዋርያው ጳውሎስ ሲደረጉ ፣ ሉቃስ አነስተኛ ሕመሞችን ፍቱን በሆኑ ባሕላዊ መድኃኒቶች ሲረዳ እንደቆየ ማሰብ ይቻላል። ጢሞቴዎስ ይሰማው የነበረው የሆድ ሕመም በፈውስ አልተወገደም ነበር ፣ ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ባሕላዊ ዘዴ እንዲጠቀም መክሮታል (1ኛ ጢሞ 5 : 23):: በሕዝቅያስ ዘመን ደግሞ መለኮታዊ ፈውስና ሕክምና በአንድ ላይ ተፈጻሚ ሲሆኑ ነው የምናየው (2ኛ ነገ 20:4 - 7):: ሕዝቅያስ እንደሚፈወስ እግዚአብሔር ተናግሯል ፣ ሆኖም ግን ኢሳይያስ ትኩስ የበለስ ጥፍጥፍ ቁስሉ ላይ እንዲደረግም አዘዘ። በዘመኑ የበለስ ጥፍጥፍ ለመድኃኒትነት ይጠቀሙበት እንደነበር ይታወቃል[9]።

ዛሬ በልምድ የምናየውም የመጽሐፍ ቅዱስን ፈለግ የሚመስል ነው። አብዛኛውን ጊዜ መለኮታዊ ፈውስ የሚፈጸመው በሕክምና የማይረዱ ከባድ በሽታዎች ላይ ነው። ጊዜያዊ ራስ ምታትና ጉንፋን ወይም በአንቲባዮቲክ ሙሉ በሙሉ ሊረዱ የሚችሉ ቁስሎች በአብዛኛው መለኮታዊ ፈውስ አይገለጥባቸውም። ይህ ሁኔታ ከመለኮታዊ ፈውስ መሠረታዊ ዓላማ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። እግዚአብሔር የሚፈውሰው በሁለት ታላላቅ ምክኒያቶች ነው። አንደኛው ምክኒያት በከፍተኛ ሕመም ለሚሰቃይ ሕመምተኛ በመራራት ነው። በሰሊሆም መጠመቂያ አጠገብ 38 ዓመታት ሲሰቃይ የቆየው ሰው መፈወስ ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ሌላው ምክኒያት የተሰበከን ወንጌል ለማጽናት በምልክትነት የሚደረግ ፈውስ ነው። በጌታ ኢየሱስና በሐዋርያት የአደባባይ አገልግሎት የተፈጸሙት አብዛኛዎቹ ፈውሶች በዚህ ዓላማ የተደረጉ ናቸው። ከነዚህ መሠረታዊ ምክኒያቶች ውጪ ፣ ሕመም ሁሉ በተዓምር እንዲፈወስ ወይም ፍቱን የሆነ መድኃኒት አልወስድም ብሎ ሰው መለኮታዊ ፈውስን እንዲጠብቅ በግልጽ የሚመራ የእግዚአብሔር ቃል የለም። እንዲያውም ይህ ዓይነቱ አቋም እግዚአብሔርን እንደመፈታተን ሊቆጠር ይችላል[10]። ሰይጣን ጌታን ሲፈትነው ከመቅደሱ ጫፍ ራሱን ወደምድር እንዲጥል ነበር የጠየቀው (ሉቃ 4 : 9 - 12):: ከቤተመቅደሱ ጫፍ ወደመሬት መውረጃ ደረጃ እያለ ራስን ወደ መሬት መወርወር እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። በተመሳሳዩ ፣ መፍትሔ የሚሰጥ የታወቀ መድኃኒት እያለ መለኮታዊ ፈውስ የግድ ይምጣ ማለት ከዚህ አይለይም።

ከነዚህ ግንዛቤዎች በመነሳት ፣ በሕክምና እርዳታ ላይ ያለ ሰው ለፈውስ ሲጸለይለት ሕክምናውን ወዲያው ማቋረጥ አለበት የሚለው አስተሳሰብ አስፈላጊ እንዳልሆነ እናስተውላለን። ጸሎት የተደረገው ስር-ነቀል ፈውስ እንዲገኝ ነው ፣ ለዚህም አገልጋዩና ሕመምተኛው አምነዋል። ሕመምተኛው እየወሰደ ያለው መድኃኒት በመለስተኛ ደረጃ ሰውዬውን በሕይወት እያኖረው ነው። ይህን የመሰለ መድኃኒት መውሰድ የሕመምተኛውን እምነት የሚያላላ አይደለም። ስለዚህም ስር-ነቀል የሆነው ፈውስ ከእግዚአብሔር እስኪፈቀድና ተፈጻሚ እስኪሆን ድረስ መድኃኒቱን ሊወስድ ይችላል ፣ አስፈላጊም ነው። ለፈውስ



ተጸለየ ማለት ፈውሱ እጅ በእጅ ተፈጸመ ማለት አይደለም። ፈውሱ ዘግይቶ ሊመጣ ይችላል ፣ ወይም ጨርሶ ላይመጣ ይችላል። አፍሮዲጡ (ፊሊጵ 2 : 26 - 27) ፣ ጳውሎስ (2ኛ ቆሮ 12 : 8 - 9) እና ጥሮፊሞስ (2ኛ ጢሞ 4 : 20) ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። ፈውስ ሲረጋገጥ መድኃኒቱን ማቋረጥ ይቻላል። ያለዚያም የሕይወት ሕልፈት እንኳን ሊያጋጥም ይችላል።

እንግዲህ መለኮታዊ ፈውስንና ሕክምናን በተመለከተ ምን ዓይነት ሚዛናዊ አሠራር መያዝ እንችላለን? ክርስቲያን ሲታመም ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዲፈውሰው ይጸልይ። ያጋጠመው ሕመም ቀላል ይሁን ከባድ ከመነሻው አይታወቅምና ለፈውሱ እግዚአብሔርን ይተማመን። እግዚአብሔርን እየጠበቀ ሳለ ፣ የሚረዳ መድኃኒት ካለ ጸልዮ መድኃኒቱን ይውሰድ። መጸለዩ እምነቱን በመድኃኒቱ ላይ ሳይሆን አሁንም በእግዚአብሔር ላይ ማድረጉን ያመለክታል ፣ መድኃኒቶችም የማይፈለግ ችግር የመፍጠር (side effect) ስላላቸውም በጸሎቱ የእግዚአብሔርንም ጥበቃ ይለምናል። ሕመሙ ቀላል ሆኖ በመድኃኒቱ የሚገታ ከሆነ እግዚአብሔርን ያመስግን። መድኃኒቱ የማይረዳው ከሆነና ሕመሙ እየባሰ ከሄደ ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወይም የፈውስ ስጦታ ያላቸው እንዲጸልዩለት አድርጎ በእምነት የእግዚአብሔርን ፈውስ ይጠብቅ። ይህን እየጠበቀ እያለ በተሻለ የሕክምና ዘዴ ሊረዳ ይችላል። ሕክምና ሙሉ በሙሉ ወይም ጨርሶ ሊረዳቸው የማይችሉ ብዙ የሕመም ዓይነቶች ስላሉ እምነትን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ማድረግ ግዴታ ነው። በዚህ ዓይነት ጥንቃቄ ስንኖር "ከአእምሮ ውጪ ብንሆን ለእግዚአብሔር ነው ፣ ባለአእምሮ ብንሆን ለእናንተ ነው" (2ኛ ቆሮ 5 : 13) ፣ የሚለው ቃል ይፈጸማል። በሰዎች ዘንድ ግልጽ የሆነውና የሚረዳውን ሕክምና አንጠቀምበትም ብለን አደጋ ውስጥ ብንወድቅ ከአእምሮ ውጪ እንደሆንን እንቆጠራለን። ለወንጌልም እንቅፋት እንሆናለን።

## ➢ የአዲስ ኪዳን የፈውስ አፈጻጸም ሂደት

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለፈውስ የተመዘገበው እጅግ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉን በዝርዝር ለማቅረብ ለዚህች አነስተኛ መጽሐፍ አያመችም። ከዚህ ይልቅ ዋና ዋና ማጠቃለያዎችን አሰፍራለሁ።

- ☞ የጌታ ኢየሱስም ሆነ የሐዋርያት ዋና ትኩረት ወንጌል መስበክ ላይ እንጂ የአካል ፈውስ ላይ አልነበረም። የጌታም ሆነ የደቀመዛሙርቱ ስብከት ርዕስ "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንሥሐ ግቡ የሚል ነበር" ፣ (ማቴ 4 : 17 ፣ 10 : 7)። የሚያስደንቀው ነገር ግን ፣ ፈውስ የስብከታቸው ርዕስ ባይሆንም እንኳን የመጡ በሽተኞች ሁሉ ይፈወሱ ነበር። ይህን ምሥጢር የሚፈታልን ሉቃ 16 : 20 ነው ፦ ትክክለኛው ወንጌል ሲሰበክ ፈውስ በምልክትነት ይከተላል። ዛሬ የሚደረገው ከዚህ የራቀ ነው፦ "ታላቅ የፈውስ አገልግሎት!" እየተባለ በአውራ መንገድ ላይ ጨርቅ ይሰቀላል። ብዙ ሕመምተኞችና ድሆች ስላሉ እነርሱን ለመሰብሰብ የሚደረግ ስልት

ይመስላል። መንፈስ ቅዱስ ግን ለሰው ስልት ስለማይገዛ ፣ የታወጀውን ያህል ፈውሱ አይገኝም። ይህ ደግሞ ለወንጌል እንቅፋት ይሆናል።

- በአዲስ ኪዳን የፈውስ አገልግሎት ውስጥ እጅ ጭኖ መጸለይ ትልቅ ቦታ ነበረው። ጌታ ኢየሱስ በመጡት በሽተኞች ሁሉ ላይ እጁን ጭኖ መጸለዩ

  የማያወላዳ መመሪያ ይሆነናል (ሉቃ 4 : 40)። በሽተኞቹ እጅግ ብዙ ሳይሆኑ አይቀርም ፣ በጅምላ የፈውስ ቃል ተናግሮ መሸኘቱ የተሻለ መንገድ ቢሆን ኖሮ ጌታ በቀላሉ ባደረገው ነበር። ሌሎችም የበዙት የጌታ ፈውሶች የአካል መንካት ነበረባቸው፡- ለምጻሙን መዳሰስ ፣ የዕውሩን ዓይን ጭቃ መቀባት ፣ የድዳውን ምላስ መንካት ፣ በደንቆሮው ጆሮ ውስጥ ጣትን ማስገባት ፣ የሕመምተኞች ኢየሱስን መንካት ፣ ወዘተርፈ። በሐዋርያትም አገልግሎት እንደዚሁ ነበረ። የጴጥሮስ እጅ ሊዳስሳቸው እድል ያላገኙ ጥላው እንዲያርፍባቸው በመንገድ ይቀመጡ ነበር (ሐሥ 5 : 15 - 16) ፣ በጳውሎስ እጅም ብዙ ተዓምራት ይደረግ ነበር ፣ ሩቅ ቦታ ላሉት ደግሞ አካሉን የነካ ጨርቅ እየተላከ ይፈወሱ ነበር። በእጅ መንካት ትልቅ መልዕክት አለው፡- የፍቅርና ለሰው ዋጋ የመስጠት ምልክት ነው። ሕመምተኛ ዘንድ ቀርቦ ስቃዩ ሲታይ አገልጋይ የበለጠ ርኅራኄ አድሮበት እግዚአብሔርን የበለጠ ሊማጠን ይችላል። ዛሬ እየተለመደ ያለው የሩቅ ለሩቅ የፈውስ አገልግሎት ይህን የአዲስ ኪዳን አሠራር ያገናዘበ አይደለም።

- ቃል በመናገር ፈውስ የተፈጸመባቸው ወቅቶች ጥቂት ናቸው። በተለይ የዕውቀትን ቃል በመናገር የተፈጸሙት የበለጠ ውስን ናቸው። በጌታ አገልግሎት
  ሦስት ጊዜ ብቻ ነው የተመዘገበው ፣ ከእነርሱም ሁለቱ ለየት ያለ ምክኒያት ነበራቸው። በማቴ 8 : 5 -13 የምናነበው መቶ አለቃው ልጁ በዚያ መንገድ እንዲፈወስ ስለጠየቀ ነው። በዮሐ 4 : 46 - 53 የምናነበው ሕመምተኛው የአንድ ቀን መንገድ ርቀት ላይ ስለነበረና ኢየሱስ ያን ሁሉ መንገድ ተጉዞ ቢሄድ ምናልባት ልጁ ሞቶ ያገኘው ስለነበረ ነው። የሞተን ከማስነሳት ይልቅ በሕይወት ያለውን መፈወስ ስለሚቀል የዕውቀትን ቃል በመናገር እንደፈወሰው ማሰብ እንችላለን። በማር 7 : 24 - 30 የተጠቀሰው የከነናዊቷ ሴት ልጅ ከአጋንንት ነፃ የወጣችበት ሁኔታ ሦስተኛው ምሳሌ ነው።

- የኤንያ ፈውስ (ሐሥ 9 : 33 - 34) እንዲሁም የልስጥራሉ ሽባ ሰው ፈውስ (ሐሥ 14 : 8 - 10) የዕውቀትን ቃል ከመናገር ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ እንደሆነ ብንወስድ ፣ መገለጡ ከግለሰቦቹ ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆኑን እናስተውላለን። በጅምላ ለብዙ ሰዎች የተነገረ አልነበረም።

- ለፈውስ የተጸለየላቸው ሰዎች ሁሉ ይፈወሱ ነበር (ማቴ 4 : 23 - 25 ፣ ሐሥ 5: 15 - 16)። ዛሬም የመፈወስ ጸጋ የተሰጣቸው አገልጋዮች



ለበሽተኞች ሲጸልዩ ለብዙዎች ከተጸለየላቸው አብዛኛዎቹ እንደሚፈወሱ መጠበቅ እንችላለን ማለት ነው። ለብዙዎች ተጸልዮ ምንም ያህል ሰዎች ባይፈወሱ "ለምን? " ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል። "በሽተኞች ስለማያምኑ ነው" የሚለው የተለመደው ምላሽ አጥጋቢ አይደለም። ምክኒያቴን በዚሁ ክፍል "የችግሩ አስከፊ ገጽታዎች" በሚለው ንዑስ ርዕስ ውስጥ አስፍሬአለሁ።

## መ) የተዛባውን የፈውስ አገልግሎት ለማስተካከል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ያለውን የፈውስ አገልግሎት ለማስተካከል የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና እረኞች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። አገልግሎቱን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ቃል ሃሳብ ከጨበጡ በኋላ ተመካክረው የማስተካከያ እርምጃዎችን ዘላቂነት ባለው አሠራር ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሚከተሉት ሃሳቦች የማስተካከያ እርምጃዎች ናሙና ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡-

➢ **የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በአጥቢያይቱ አገልጋዮች ማኪያሄድ**

ይህ እርምጃ ለያዝነው ርዕስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ችግሮች መፍትሄ ይሆናል። ከውጪ ተጋብዘው የሚመጡ አገልጋዮች በገዛ ቤተ ክርስቲያናቸው የማያደርጉትን ልምምድ በሌላው ቤተ ክርስቲያን እንደሚያደርጉ ይታወቃል። በቤተ ክርስቲያናቸው መሪዎች ላይ ያላቸውን ብሶት እንኳን ተጋብዘው በሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚሰብኩ አሉ! አንድ ጊዜ መድረክ ይዘዋልና የጋባዥ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያደርጉት ግራ ነው የሚገባቸው። ረጋ ብለን ብናስበው ፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉትን የጸጋ ስጦታዎች ይለግሳል[11]። የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች የአገልገሎት መድረክ ሲያገኙ ነው በጸጋቸው እየጎለመሱ የሚሄዱት። በአሁኑ ጊዜ የተያዘው ፈሊጥ ግን ከሳምንት እስከ ሳምንት ፣ ከወር እስከወር ፣ ከውጪ የሚመጡ አገልጋዮችን መጋበዝ ነው ፣ በተለይም የዕውቀትን ቃል መናገር ፣ ወይም የትንቢት ፣ ወይም የፈውስ ስጦታ አላቸው ተብለው የሚታሰቡትን። የቤተ ክርስቲያኑ አንገብጋቢ ፍላጎት ይህ መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ የተጠቀሱት ስጦታዎች ጨርሶ የሌላቸውም ሰዎች ማስመሰል ይጀምራሉ።

የአጥቢያይቱ አገልጋዮች በአጥቢያይቱ አዘወትረው ቢያገለግሉ ማንነታችውና ያላቸውም ጸጋ ስለሚታወቅ በጥንቃቄ ያገለግላሉ። በአገልግሎታቸው ነቀፌታ ቢገኝ ለመጠየቅ ፣ ጥሩ ፍሬም ቢገኝ ለመመስገን በቅርብ ይገኛሉ። በመደበኛ ለሚሰጡት አገልግሎትም ቀለብ የተመደበላቸው ስለሆነ ስጦታ የመቀበል ተስፋም አገልግሎታቸውን አያዛባውም። ከሁሉ በላይ ደግሞ በታማኝነት ሕዝባቸውን እያገለገሉ ስለሆነ እግዚአብሔር ጸጋቸውን

ያሳድገዋል። ለራሳቸው ሕዝብም ሸክም ስላላቸው እግዚአብሔር ራዕያቸውን እያሰፋ ሕዝቡን ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ የሚያሳድግ አገልግሎት በረዥም ጊዜ ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተለያየ ልምድና አመለካከት በሚመጡ አገልጋዮች ከወር እስከወር የምትገለገል ከሆነ ግን የዘረዘርናቸው በረከቶች አይገኙም ፣ በተቃራኒው ግን አዳዲስ ልማዶችን በማስተናገድ ሕዝቡ ይንገላታል ፣ ለአስመሳዮችም ማታለል ሊጋለጥ ይችላል። የአጥቢያይቱ አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያናቸው አዘውትረው ያገልግሉ ስንል ከውጪ ሌላ አገልጋይ ጨርሶ አይጋበዝ ለማለት አይደለም። በወር ወይም በሁለት ወር አንድ ጊዜ ከውጪ አገልጋይ ሊጋበዝ ይችላል። በዚህ ሁኔታ የሚጋበዘው አገልጋይ የበሰለና ማንነቱ በሚገባ የሚታወቅ መሆን አለበት። እንደዚህ ዓይነቱ አገልጋይ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባላት ብቻ ሳይሆን መሪዎቿንና አገልጋዮቿን ሁሉ ሊያስተምር የሚችል ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ባላት ጸጋ ላይ በጎ አስተዋፅዖ ያደርጋል ማለት ነው።

## ➢ የፈውስ አገልግሎት የአዲስ ኪዳንን ፈለግ እንዲይዝ ማድረግ

በግልጽ እንደተረዳነው ፣ መደበኛ የአዲስ ኪዳን የፈውስ አገልግሎት እጅ በመጫን የሚከናወን ነው። ይህ አሠራር ደግሞ ጊዜ የሚወስድ ነው። ከዚህ የተነሳ ከተለመደው የእሁድ አምልኮ ፕሮግራም በኋላ አመርቂ የፈውስ አገልግሎት ለመስጠት አያመችም ፣ ከዚያ ይልቅ በሌላ ቀን የጸሎትና የፈውስ ፕሮግራም መመደቡ የተሻለ ነው። በዚህ ፕሮግራም የሚያረካ የአምልኮ ፕሮግራም ከተደረገ በኋላ እምነትን የሚገነባ የእግዚአብሔር ቃል ይነገራል። ከዚያም አጥጋቢ የሆነ ምልጃና ጸሎት ይደረጋል። ይህ እየተደረገ እያለ ሕመምተኞች ተጠርተው የፈውስ ጸጋ ያላቸውና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እጆቻቸውን ጭነው ይጸልዩላቸዋል። ጸሎቱ እየተካሄደ ሳለ አንዳንድ ሕመምተኞችን በሚመለከት የዕውቀት ቃል ሊገለጥ ይችላል፦ ፈውስን የሚያጸና ቃል ሊሆን ይችላል ፣ ጌታ የዓይነ ስውሩን ዓይን በጭቃ እንደቀባ ዓይነት ምሪት የሚሰጥ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ሰውየው ሕይወቱን እንዲያስተካክል የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ከጌታ እንደመጣው መመሪያ አገልጋዩ ይታዘዛል። አገልጋይ ወደ ሕመምተኛው ቀርቦ ሲጸልይ ሌላው ሊሆን የሚችለው ከክፉዎች መናፍስት ጋር የተያያዘ ሕመም ከሆነ መገለጡ ነው። በዚህኛው ሁኔታ ትክክለኛው እርምጃ ክፉዎችን መናፍስት ገሥጾ ማስወጣት ይሆናል። መለስተኛ የአእምሮ መታወክ ያለባቸው ቢያጋጥሙ ለፈውስ ከመጸለይ ይልቅ አስቀድሞ ተገቢውን የምክር አገልገሎት ማድረግ ያስፈልጋል። ከፍተኛ የአእምሮ መታወክ ያለባቸው ለምክር አገልግሎት መተባበር አይችሉም። ለዚህ ሁኔታ አግባብ የሚሆነው ፣ ከባለሙያዎች እንክብካቤ ጋር ለፈውስ ብርቱ ምልጃ ማድረግ ነው። ለእያንዳንዱ ሕመምተኛ እንደ ሁኔታው ተገቢ አገልግሎት ለመስጠት ይህ የአዲስ ኪዳኑ የፈውስ አገልገሎት ፈለግ ወሳኝ ነው። ከእሁድ መልዕክት በኋላ በችኮላ በሚወረወር የፈውስ አዋጅ (እውነተኛ ከሆነ ማለት ነው) ለእያንዳንዱ ሕመምተኛ የሚደርስ አመርቂ አገልግሎት መስጠት አይቻልም።



የሚጸለይለት ሕዝብ ብዛት ከአቅም በላይ እስካልሆነ ድረስ በጀማ ስብከተ ወንጌል ወቅትም ተመሳሳይ አሠራር ማስፈን ይቻላል። የወንጌል ቃል ከተሰበከ በኋላ ሕመምተኞች ለጸሎት ሊጠሩ ይችላሉ። ከየቤተ ክርስቲያኑ የተውጣጡ የተመሰከረለት የፈውስ ስጦታ ያላቸውና የየቤተ ክርስቲያኑ ሽማግሌዎች እጅ በመጫን ወንጌል ሰባኪውን እየረዱ ለእያንዳንዱ በሽተኛ ሊጸልዩ ይችላሉ። የሕዝቡ ብዛት ከአቅም በላይ ሲሆን በጅምላ ለፈውስ መጸለይ ግዴታ ይሆናል።

## ➢ ለፈውስ ከተጸለየ በኋላ በቂ ምክር መስጠት

የመጀመሪያው ምክር የተጸለየላቸው ሰዎች ፈውስን በእምነት እንዲቀበሉት ማስረዳት ነው። ጌታ ኢየሱስ "ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" (ማር 11 ፡ 24) ባለው መሠረት ይህ ምክር አግባብ ነው። ሆኖም ግን ምክሩ ሲሰጥ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። እየተባባሰ ባለ ሕመምና ለውጥ በማያሳይ እንደ ሀይነ-ስውርነት ባለ ሕመም መካከል ልዩነት ማድረግ ያስፈልጋል። ለውጥ የማያሳየውን ዓይነት ሕመም በተመለከተ ላልተወሰነ ጊዜ ፈውስን በእምነት መጠበቅ ይቻላል። እየተባባሰ ባለ ሕመም ላይ ግን የጊዜ ገደብ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ካልተደረገ ሕመምተኛው ተገቢውን ዝግጅት ሳያደርግ ወደ ሕልፈት ሊደርስ ይችላል። በሕክምና የሚገኝ ፈውስን ምሳሌ አደርገን ብንወስድ ፣ የተወሰደው መድኃኒት የሚሠራ ከሆነ በቀናት ውስጥ ቢበዛ በሳምንትና በሁለት ሳምንት ውስጥ ለውጥ መታየት ይጀምራል። መለኮታዊ ፈወስም ተመሳሳይ ባሕርይ አለው። ቅጽበታዊ የሆነው ተዓምራዊ ፈውስ ምንም አያነጋግርም። አንዳንድ ፈውሶች ግን ልክ በመድኃኒት እንደሚሆን ደረጃ በደረጃ የሚፈጸሙ ናቸው።

እየተባባሰ የሚሄድ ሕመም ያለው በሽተኛ ከተጸለየ በኋላ እንደሕመሙ አጣዳፊነት በቀናት ወይም በአንድና በሁለት ሳምንት ውስጥ የመሻል ለውጥ ካላየ አልተፈወሰም ማለት ነው። ተፈውሻለሁ እያለ እስከመቃብር ድረስ መሄዱ ትርጉም አይሰጥም። በቂ ጊዜ ተሰጥቶ ለውጥ ካልታየ ሕመምተኛው ካገለገሉት ሰዎች ጋር ተገናኝቶ ተጨማሪ አገልግሎት ማግኘት ያስፈልገዋል። የተጸለየለት ሰው ፈውስ የማይቀበልበት የተለያዩ ምክኒያቶች አሉ። የበደለን ይቅር አለማለት የተለመደ ምክኒያት ነው ፣ እንደዚሁም ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት። ሕመምተኛው በባዕድ አምልኮ ይሳተፍ ከነበረ ከሰይጣን ጋር ያለውን ግንኙነት በይፋ አውግዞ ካላቋረጠ ፈውስ አይኖርም። ይህንን የመሳሰሉ የፈውስ እንቅፋቶች የሚገለጡት አገልጋዮች ሕመምተኛውን እያዳመጡት ሲያማክሩት ነው። በትልቅ ሁኔታ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ያጋጠመውን ዓይነት "የሥጋ መውጊያ" የሚሆን ዓይነት ሕመም ሊያጋጥማቸው ይችላል[12]። እንደዚህ ዓይነቱ ሕመም በጸሎት አይፈወስም። የአስም በሽታ የነበረው አንድ አገልጋይ አውቃለሁ። ለአገልግሎት መድረክ ላይ ሲወጣ ሰሞኑን ሁሉ ሲያፍነው የነበረው አስም ይለቀውና በታላቅ ኃይል ያገለግላል። ከመድረክ ሲወርድ አስሙ ይቀበለዋል! በሕመሙ ምክኒያት አገልግሎቱ አልተገታም ፣ የሕመሙ አለመፈወስ ደግሞ ከጌታ እጅ በታች ራሱን ዝቅ እንዲያደርግ የሥጋ መውጊያ በመሆን ያገለግለዋል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የመጣው ሕመም ወደ መንግሥተ-ሰማያት የመሸጋገሪያ ድልድይ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈቅዳል። ጌታ ይህን የሚያደርገው ለሰውየው በማሰብ ነው ፣ ኢሳይያስ በግልጽ እንዳስቀመጠው:-

> "ጻድቅ ይሞታል ፣ ይህን ግን ማንም ልብ አይልም ፣ ለእግዚአብሔር ያደሩ ሰዎች ይወሰዳሉ ፣ ጻድቃን ከክፉ ይድኑ ዘንድ መወሰዳቸውን ማንም አያስተውልም።" (ኢሳ 57 ፡ 1)

ግልጽ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ካልተገኘ በስተቀር ፣ በጠና ለታመመ ሰው ጸልዮ "ተፈውሷል" በማለት የድፍረት ማረጋገጫ መስጠት ትክክል አይደለም። ከዚያ ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማጣራቱ ማስተዋል ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳያጣሩ ፣ እግዚአብ.ሔር ሊወስደው ያቀደን ሰው እንዲመለስ የሙጥኝ ማለት ሕመምተኛውን ለማያስፈልግ የተራዘመ ስቃይ መዳረግ ይሆናል ፣ ቤተሰብም ያለአግባብ ይጉላላል። አንዳንድ ጊዜ ዕድሜ የጠገቡ አዛውንት ወደመጨረሻው ሲደርሱም ካልተፈወሱ ብሎ የሙጥኝ የሚባልበት ጊዜም አለ። ይህ ዓይነቱ ተማፅኖ የሕሊና ሚዛን የጎደለው ነው። በዚህ ዓይነቱ ጸሎት አምርሮ መሰለፍ እግዚአብሔር በሰው ተፈጥሮ ያስቀመጠውን ሕግ መቃወም ይመስለኛል!

እንግዲህ ከሕመምተኛው ጋር በሚደረግ ምክክር ለፈውስ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮቹ ከታወቁ እነዚህ እንዲስተካከሉ ተደርጎ በድጋሚ ይጸለያል። በተረፉት ሁኔታዎች መለኮታዊ ፈውስ የማይጠበቅ ሲሆን ግለሰቡም ሆነ ቤተሰብ ለሚመጣው ሕልፈት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ በጥበብ ይመከራሉ። ሌላው መዘንጋት የሌለበት ፣ ፈውስ በእምነት እየተጠበቀ ሳለ ፣ የፈውስ ተስፋ ይኑርም አይኑርም ተገቢው የሕክምና እርዳታ መቀጠል ይኖርበታል። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ከፍ ባለው ክፍል አብራርቻለሁ።

ሌሎች መመከር ያለባቸውን ሁለት ነጥቦች ባጭሩ አስቀምጣለሁ። አንዱ ከሕክምና ጋር የተያያዘ ነው። መድኃኒት በቋሚነት እየወሰዱ ያሉ ሰዎች ለፈውስ ስለተጸለየላቸው መድኃኒቱን ማቋረጥ የለባቸውም። ፈውሱ ተግባራዊ መሆኑን ሲያረጋግጡ ነው ማቋረጥ የሚችሉት። ሌላው ከጸሎት በኋላ መለኮታዊ ፈውስ እየተጠባበቁ ሳሉ ማንኛውንም ይረዳል የተባለ መድኃኒት እንዲወስዱ ሊመከሩ ይገባል። ለነዚህም ጉዳዮች "መለኮታዊ ፈውስና ሕክምና" በሚለው ክፍል ማብራሪያ ሰጥቻለሁ። ሁለተኛው መመከር ያለበት ጌታን የማያውቁ ሰዎችን በተመለከተ ነው። ከጌታ ቸርነት የተነሳ የወንጌል ነገር በደንብ ያልገባቸው ሰዎችም ሊፈወሱ ይችላሉ። እነዚህና በቅርቡ ጌታን የተቀበሉ ሰዎች ተገቢውን የክትትል ትምህርት እንዲያገኙ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ጌታም በተደጋጋሚ ያደርግ እንደነበረው ተመልሰው ኃጢአትን እንዳይሠሩ መመከር አለባቸው።



## ➢ ለፈውስ ከተጸለየ በኋላ ክትትል ማድረግ

ክትትሉ ሕመምተኞችንም አገልጋዮችንም ይመለከታል። ሕመምተኞችን በተመለከተ ግልጽ የሆነ ፈውስ የተፈጸመላቸው እንዲመሰክሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ቅጽበታዊ ፈውስ የሆነላቸው በዚያው በፈውሱ ፕሮግራም ወቅት እንዲመሰክሩ ይደረጋል። ደረጃ በደረጃ የሚገለጥ ፈውስ ሲጠናቀቅ ባመቺ ጊዜ እንዲመሰክሩ ይደረጋል። ይህ ዓይነቱ ምስክርነት ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ከማምጣቱም በተጨማሪ የምዕመናን እምነት እንዲያድግ አስተዋፅዖ ያደርጋል። በተቻለ መጠን ፈውሱ በሕክምና ምርመራ መረጋገጡ አስፈላጊ ነው። የሕክምና ምርመራ ማረጋገጫ ሲኖር የሚሰጠው ምስክርነት ተቃዋሚዎችን እንኳን ሊያሳምን ይችላል። የምርመራው ውጤት ሕመሙ እንዳልተወገደ የሚያሳይ ከሆነ ደግሞ ከመመስከር መቆጠብ ያስፈልጋል። ተጸልዮላቸው ያልተፈወሱ ሕመምተኞችም ፣ ከፍ ብሎ ባሉት አንቀጾች እንደዘረዘርኩት ቀጣይ አገልግሎት ሊደረግላቸው ያስፈልጋል። በነዚህ ምክኒያቶች ለፈውስ የተጸለየላቸው ሕመምተኞች ምን እንዳጋጠማቸው ለቤተክርስቲያን ሪፖርት እንዲያደርጉ ለቤተዘመድ መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል።

በአገልጋዮች ላይ የሚደረገው ክትትል እውነተኛ ጸጋ ያላቸውንና አስመሳዮችን ለመለየት እንዲያስችል ነው። በምዕራፍ 1 ወስጥ እንደዘረዘርኩት ጸጋ የሚለየው በፍሬ ነው። አንድ የፈውስ ስጦታ አለኝ የሚል አገልጋይ ለብዙ ሕመምተኞች ጸልዮ አንዳቸውም ባይፈወሱ ይህ ሰው አለኝ ይበል እንጂ የፈውስ ጸጋ የለውም። ተገቢው ክትትል ተደርጎ የፈውስ ፍሬ ካልታየ አገልጋዩ ሊመከርና ራሱን እንዲመረምር ሊደረግ ያስፈልጋል። ምክርን የማይቀበል ከሆነ ደግሞ ከቤተክርስቲያን የፈውስ አገልግሎት መድረክ ሊታገድ ያስፈልጋል። በአንጻሩ ደግሞ መልካም ፍሬ የተገኘበት አገልጋይ ጸጋውን እንዲያሳድግ ሊበረታታ ያስፈልገዋል። በዚህ ዓይነት ኃላፊነት በተሞለበት መንገድ ሥራው ሲሠራ አስመሳዮች ይታቀባሉ ፣ እውነተኛ ጸጋ ያላቸው ደግሞ እየበረከቱና እያደጉ ይሄዳሉ።

==================================================

### ማስታወሻ


1. ፈውስ የሚገኘው በመገለጥ ብቻ ነው ያለው ማነው? "ተናገር" ጋዜጣ ቁ 6 /93 ነሐሴ 1993.
2. ማር 10 ፡ 51 - 52 ፣ ሉቃ 5 ፡ 12 - 13 ፣ 17 - 20 ሉቃ 9 ፡ 43 - 48 ፣ ሉቃ 17 ፡ 11 - 19
3. ሮሜ 6 ፡ 3 - 7
4. ኢሳ 11 ፡ 1 - 2 ፣ 61 ፡ 1 - 2
5. መሳ 6 ፡ 36 - 40 ፣ 2ኛ ነገ 20 ፡ 8 - 11
6. ማቴ 10 ፡ 32 - 33
7. ኤፌ 4 ፡ 11
8. ያዕ 5 ፡ 14 - 16
9. Carson, D.A. 1995. New Bible Commentary, 4th Ed P. 381
10. Grudem, W., 1994 Systematic Theology, P. 1064
11. 1ኛ ቆሮ 1 ፡ 7
12. 2ኛ ቆሮ 12 ፡ 7 - 10

## የማጠቃለያ ማሳሰቢያ

ይሁዳ በዘመኑ ለነበሩ ክርስቲያኖች ስለደኅንነት በረከት ሊጽፍላቸው ጓጉቶ ሳለ ፣ "ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለተሰጠው እምነት" እንዲጋደሉ በመምከር እንዲጽፍላቸው መንፈስ ቅዱስ አስገደደው። እኔም ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ስጽፍ ተመሳሳይ ሸክም በልቤ ተሰምቶኝ ነው። መጽሐፏ አጭር እንድትሆን ያደረግሁትም ዋና ነጥቦችን በግልጽነት በማስቀመጥ የሚመለከታቸው ሁሉ ሳይታክቱ እንዲያነቧት በመመኘት ነው። ምናልባት አንዳንዶቻችሁ ኃይለ-ቃል ተጠቅመሃል ብላችሁኝ ይሆናል። ለዚህ ያለኝ ምላሽ ይሁዳን ምሳሌ አድርጌ ማቅረብ ነው። ከእኔ ጋረ ሲወዳደር ይሁዳ በበለጠ ሁኔታ ምርር ያለ ኃይለ-ቃል ተጠቅሟል። እንደ እኔ ግምገማ ያለንበት ሁኔታ ኃይለ-ቃልን መጠቀም ብቻ ሳይሆን ልብስ ቀዶ ፣ አመድ ነስንሶ በአደባባይ "ኡ! ኡ!" የሚያሰኝ ነው።

እንግዲህ በተቻለኝ መጠን መልዕክቴን በግልጽነትና በድፍረት አቅርቤአለሁ። አንባቢው በሚመለከተው አቅጣጫ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ በጌታ ፍቅር እለምናለሁ። የእግዚአበሔርን ቃል በውል ካለማወቅ የተነሳ በጠቀስናቸው የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ላይ ስህተት የምታደርጉ ወገኖች በቶሎ ተመለሱ። አውቃችሁ የዚህን ዓለም ጥቅም ለማግኘት በመፈለግ ጸጋ ሳይኖራችሁ በማስመሰል ቤተ ክርሰቲያንን እያጎሳቆላችሁ ያላችሁትን አስጠነቅቃለሁ፡- "ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ፣ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" ዓለምን ለማትረፍ ብላችሁ ነፍሳችሁን እያጎደላችሁ ስለሆነ ፣ ጌታ ኢየሱስ በሚገለጥበት ጊዜ ለእናንተ ድንጋጤ ይሆናልና። በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችንና እረኞችን በጌታ ፍቅር ፣ በትህትና አሳስባለሁ። ቤተ ክርስቲያን በሥርዓት እንድትመራ የማድረጉ ቁልፍ ኃላፊነት በእናንተ እጅ ነው ያለው። ሥራችሁን በዕውቀት ለመሥራት ይረዳችሁ ዘንድ ይህችን ጽሑፍ በተቻለ ግልጽነት አቅርቤላችኋለሁ። መልዕክቷን ይዛችሁ ፣ በተጨማሪም የጌታን ቃል በስፋት አጥንታችሁ ፣ የጌታን ቤት እያበላሹ ያሉትን ግድፈቶች ለማስተካከል በአንድ ልብ ሆናችሁ ወገባችሁን ታጥቃችሁ ቁሙ። ይህን ፈጥናችሁ ባታደርጉ በቤተ ክርስቲያኖቻችሁ ላይ የበረከት ጀምበር ትጠልቃለች። ጌታ ኢየሱስ በሚገለጥበትም ጊዜ ታፍራላችሁ ፣ እፍረታችሁም የዘለዓለም እፍረት ይሆናል።

በጌታ በሳል የሆናችሁትን ወገኖች ደግሞ እለምናለሁ። የተረዳሁትን በግልጽነት አቀረብሁ እንጂ ሁሉን ያወቅሁ ሰው አለመሆኔን እገነዘባለሁ። ባቀረብኳቸው ነጥቦች ላይ እርምት ወይም ምክር ቢኖራችሁ በአድራሻዬ ጻፉልኝ ወይም ስልክ ደውሉልኝ።